ሐምሌ 2010

የመንፈሳዊ መዝሙር ጥራዝ

በይምርጎነ ክርስቶስ (መንግስተአብ ብርጎነ)



አእምሩ ኀመ ተሰብሐ እግዚአብሔር በጻዲቁ መዝ4÷3

ማውጫ

ተ/ቁ.	ርዕስ	ተ/ቁ.	ርዕስ
1.	ላመስግንህ የኔ ጌታ	22.	ስለ ማይነገር ስጦታው
2.	ምን ሰማህ ዮሐንስ	23.	ጥሪህም ድንቅ ነው
3.	አዳነኝ ጌታ	24.	ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን
4.	ምስጉን ነው	25.	ኪዳነ ምህረት
5.	ኑ ለምስጋና እንተባበር	26.	እውነተኛ ሰላም
6.	ቸርነትህ ነው	27.	አቡነ አረጋዊ
7.	አይሸሽግ እውነቱ	28.	እግዚአብሔርን አመስግኑ
8.	ከወገኔ ጋራ እዘምራለሁኝ	29.	በምን በምን እንመስላት
9.	የደማስቆ ምርኮኛ ነኝ	30.	ነዪ ነዪ
10.	አለና ሚካኤል	31.	ለማርያም
11.	ትንሳኤሽን ያሳየን	32.	በሃዘኔ ደራሽ ነሽ
12.	ቸርነትህ ብዙ	33.	የሥላሴን መንበር
13.	ምስክርነቱን ገለጸ	34.	ትህትናሽ ግሩም ነው
14.	በስመ አብ ወወልድ መንፈስ ቅዱስ	35.	እመ ብርሀን
15.	ሰአሉ ለነ	36.	ያሬድ ካህኑ
16.	አንቺን የያዘ ሰው	37.	ውዳሴ ማርያም
17.	ቅዱስ ሚካኤል	38.	ጎሳ ልብየ
18.	እግዚአብሔርን ጠራሁት	39.	አስታርቂኝ
19.	እልል በሉ	40.	ሀያል ሀያል
20.	ባክኛለሁና	41.	ለምኚ
21.	ልቤ በእግዚአብሔር ጸና	42.	አዘክሪ ድንግል

43.አንደበቴም ያውጣ

44.ገድሉ ታምራቱ

45.ስምህ በሁሉ

46.እመቤቴ የአምላክ እናት

47.የሃይማኖት ፍሬ

48.ናርዶስ ቀጺመታት

49.የስሙ ትርጓሜ

50.ወላዲተ አምላክ

51.ሥላሴን አመስግኑ

52.ሁሉም ነገር ሆነ

53.መነነ

54.ባሕራንኒ

55.ኦ ክርስቶስ

56.ነዓ ነዓ

57.ዮም ፍስሐ ኮነ

58.ናና ሚካኤል ናና

59.አምላክ ባከበራት

60.ደጅ ጠናው

61.አባ ሳሙኤል

62.የያሬድ ውብ ዜማ

63.ስምሽን ጠርቼ

64.ጽርሐ አርያም

65.ተ/ሃይማኖት ጸሃይ

66.ክንድህን እጠፍ

67.ይበራል በክንፉ

68.የፍቅር እናት

69.ባለ ውለታዬ

70.ማርያም ማርያም ብዬ

71.ወደ ቀድሞ ነገር

72.እናት አለኝ

73.እረድተሀል እና

74.ደጉ መልአክ

75.አለ ለኔ

76.በማህጸን ቅኔ

77.ሞገድ ሲመታኝ

78.ተ/ሃይማኖት ባህታዊ

79.ገብርኤል ስለው ሰምቶ

80.ገና እንዘምራለን

81.አረሳት ኢትዮጵያን

82.ያዕቆብ ከቤርሳቤ

83.ገብረ ሕይወት

84.በአለት ላይ ነውና

85.አባ አባ

86.ስድቤን አርቀሽ

87.ቢያበሉኝ ቢያጠጡኝ

88.የልቤን ሁሉ

89.በጎ መአዛ

90.ጎይሌ ብርታቴ

91.ገብርኤል ሀያል

92.ሰዎች እንዘምር

93.ያላንቺ ማን አለኝ

94.አ ሚካኤል

95.መጣው ተክልዬ ልሳለምህ

96.ሰላም ለኪ እያለ

97.ቸሩ ሆይ

98.ማርያም እንወድሻለን

99.አማን በአማን

100.ድንግል ማርያም

101.የመስቀሉ ፍቅር

102.እንዲህ እናምናለን

103.በዘባነ ኪሩብ

104.አ ማርያም

105.እመቤቴ ማርያም

106.ይዌድስዋ

107.ክነፈ ርግብ

108.ነአምን በአብ

109.የኪዳን ጽላት

110.አንቲ ውእቱ

111.ያከበርዋ ለሰንበት

112.ቤዛ ቤዛ

113.አባ ማርቆስ

114.ርኢክዋ ለቤተክርስቲያን

115.ኢትዮጵያ ታበጽህ

116.ኪሮስ አቡነ

117.አባ አባ

118.ለሀገሪትነ ሰላማ

119.ለተ/ሃይማኖት ጻዲቅ

120.ነይ ነይ

121.እመቤታችን ማርያም

122.አ አባ

123.መሰረተ ዜማ

124.ሰቢኮ ለወልድ

125.ጊዮርጊስ ሃያል

126.መልአከ ሰላምነ

127.ካህናት ይብልዋ

128.እምነ እምነ

129.ንጽህይተ ንጹሀን

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።።

❶ ላመስግንህ የኔ ጌታ

©ሊ/መ/ቀ/ ምንዳዬ ብርሃኑ

ላመስግንህ የኔ ጌታ ላመስግንህ

ልቀኝልህ የኔ ጌታ ልቀኝልህ

ህይወቴ ነው ዝማሬ ትሩፋቴ

የሰጠኸኝ እንዳከብርህ አንተ አባቴ

... ከእኔ የሆነ የምሰጥህ ባይኖረኝም

ከሰጠኸኝ ያንተን መስጠት አይከብደኝም

ጥበቤ ነህ የምስጋና መሰረቴ

ዝማሬዬን ያፈሰስከው በህይወቴ

ተተተአንደበቴን የቃኘኸው ለምስጋና

ተተተይኸው ውሰድ ቅኝትህን እንደገና

...ባዶ እኮ ነኝ የኔ ጌታ ምን ልቅዳልህ

በእጆቼ ላይ አንዳች የለኝ የምሰጥህ

ላንተ ክብር የሚመጥን ህይወት የለኝ

ዝማሬዬን በቸርነት ተቀበለኝ

...ከምድር ላይ ከአፈር ስትፈጥረኝ

ከምስጋና የተለየ ምን ስራ አለኝ

ቀን እና ሌት በመቅደስህ እቆማለው

አምላኬ ሆይ ሳወድስህ እኖራለው

...እዝራ ስጠኝ የከበረ መሰንቆህን

ዳዊት ስጠኝ የሚፈውስ በገናህን

መዝሙር ቅኔ ተምሬያለው ከአባቶቼ

ዘምራለው በአንተ ፍቅር ተነክቼ

2 ምን ሰማህ ዮሐንስ

©ሊ/መ/ ይልማ ሃይሉ

ምን ሰማህ ዮሐንስ በማህጸን ሳለህ (2)

ህጻን ሆነህ ነብይ ለክብር የተጠራህ (2)

እንደ እንቦሳ ጥጃ ያዘለለ ደስታ (2)

ምን አይነት ድምጽ ነው ምን አይነት ሰላምታ (2)

...ከተፈጥሮ በላይ ያስገደህ ክብር

እዴት ቢገባህ ነው የአምላክ እናት ፍቅር (2)

ሌላ ድምጽ አልሰማም ከእንግዲህ በውሃላ

ለውጦኛልና የሰላምታ ቃሏ (2)

...በረሃ ያስገባህ ለብዙ ዘመናት

ምን ያለ ራእይ እንዴት ያለ ብስራት (2)

እንደ አዲስ ምስጋና ስልቱ የተዋበ

ተደምጦ የማያውቅ ጭራሽ ያልታሰበ (2)

...ከሴት ከተገኙ ከደቂቀ አዳም

ድንግል ስለሆነ በህይወቱ ፍጹም (2)

ከማህጸን ሳለ ተመርጦ በጌታ

ለማዳመጥ ቢቃ የኪዳን ሰላምታ (2)

❸ አዳነኝ ጌታ

©ሊ/መ/ቀ/ ምንዳዬ ብርሃኑ

አዳነኝ ጌታ አዳነኝ

ፈወሰኝ ጌታ ፈወሰኝ

እግዚአብሔር አዳነኝ

ሃጢያተኛውን ወደደኝ

...ያልፋል ያላልኩት አልፎልኝ አይቼ

በእንባ ታጠብኩኝ ከድቅድቅ ወጥቼ

እንግዲህ ላንተ ምስክር ሆኛለው

<u>ስራህን ለአለም ሁሌም እነግራለው</u> (2)

ክንድህ ብርቱ ነው ደካማን ለመርዳት

ታውቅብታለህ የዛለን ማበርታት

አይኔን ከሰዎች ማራቄ ጠቅሞኛል

ደጅህ ወድቄ መኖር ተሸሎኛል

...ሃዘኔን ማቅ አውልቀህ ጣልክልኝ

ሞቴን ስጠብቅ እድሜ ጨመርክልኝ

ከአልጋዬ ላይ አነሱኝ እጆችህ

<u>ተፈውሻለው ዛሬም በምህረትህ</u> (2)

ቃልህ ጽኑ ነው ዳግም ይጠግናል

ጎባጣ አቅንቶ ሸባውን ተርትፎል

ህይወቴ ባንተ ዛሬ አዲስ ሆናለች

በክብር መዝገብ በእጅህ ተጽፋለች

...የሃሰትን ፍርድ ጌታ ቀለበስከው

ተጽናንቷል ባንተ ያ የተገፋ ሰው

የግፍን ጽዋ አራቅከው ከፊቱ

በእጁ ላይ የለም ዛሬ ሰንሰለቱ (2)



ከላይ የቀጠለ

በሃማ መስቀል መርዶኪዮስ የለም

የናቡቴ ደም በከንቱ አልቀረም

የእውነት ዳኛ ጌታ ስትመጣ

የሃሰቱ ሰው ግፈኛው ተቀጣ

4 ምስጉን ነው

©ሊ/መ/ቀ እንግዳወርቅ በቀለ

ምስጉን ነው የተወሰገነ

ባሪያውን እኔን ይቅር ያለ

ይመስገን ይመስገንልኝ

ጎጆዬን አምላክ ሞላልኝ

...እጅህ ሰፊ እንደሆነ አውቃለው ጌታዬ

የጎደለው ሞልቷል ይድረስ ምስጋናዬ

ያጣሁትን ካንተ አግኝቻለው

ሁሉም ነገር ለበጎ ብያለው

...ማቄን የቀደደ ደስታን አስታጠቀኝ

ባዶ የነበርኩኝ ሁሉ ተሰጠኝ

ሰጪም ነሺም እግዚአብሔር ብቻ ነው

የሰው ድርሻ በር ማንኳኳት ነው

...እከፋለው እንጂ እኔ አልጨነቅም

መሰረቴ አንተ ነህ ከቶ አልናወጽም

ስትሰጠኝ የሚታየውን

እንዳትነሳኝ የዘላለሙን

...ቢሰጥ አያልቅበት ለጋስ ክቡር ጌታ

ሁሉን ከወነልኝ በልዩ ችሎታ

ድሆች ስንሆን ሁሉ አለንና

አምላካችን ይድረሰው ምስጋና

❺ኑ ለምጋና እንተባበር

©ሊ/መ/ቀ ምንዳዬ ብርሃኑ

ኑ ለምስጋና እንተባበር ኑ አንድ እንሁን በሱባኤ

ኑ በመቅደሱ እናምልከው እንመስርት አንዲት ጉባኤ

...ከያሬድ ጋር እናወድስ ከዳዊት ጋር በገና እንምታ

ኑ ለሰአታት እንነሳ ከጊዮረጊስ ጋር እንበርታ

ከተከልዬ ጋራ እንስበክ ከላሊበላ ጋር እንገነባ

ከሕርያቆስ ጋር ጋር እንቀድስ ከአቡኤ ጋር ሱባኤ እንግባ

...ከሳባ ጋር ጥበብ እናምጣ ከአሮንም ጋራ ጸሃይ እናቁም

ከአረጋዊ ጋራ እንድንጸልይ ከእንባቆም ጋር እንመስክር

ከሰላማ ጋራ እንተርጉም ከኤስጥሮስ ጋራ እንመርምር

ከገላነሽጋራ እንድንቀኝ ከሃይመት ጋር እንስተምር

...ነፃ በምታወጣ በኢየሩሳሌም ከተማ

ከጽዮን ልጆች ጋራ መዝሙራችን እንዲሰማ

አንድ ሆነን በቀኝ እንድንቆም ከበኩራት ማህበር ጋራ

አንድ ሆነን እናገልግል አንድ ሆነን ዛሬ እንስራ

6 ቸርነትህ ነው

© ሊ/መ/ቀ ምንዳዬ ብርሃኑ

ቸርነትህ ነው ያደረሰኝ እስከ ዛሬ

ቸርነትህ ነው የጠበቀኝ እስከ ዛሬ

ላመሰግንህ የኔ ጌታ በዝማሬ

...መከሊቴን ቀብሬ ባሳዝንህ ሙብራቴንም ይዤ ባልጠብቅህ

በታላቅ ይቅርታ እንዳትረሳኝ በፍቅር ጎብኝትህ ከሞት አውጣኝ

ከቤትህ እርቄ መች ጠገብኩኝ በረሃብ በእርሳት ተቸገርኩኝ

አምናለው አምላኬ እንድትምረኝ ለይቅርታ መጣው ተቀበለኝ

...አንዳች እንደሌለኝ አውቀዋለው ባንተ ቸርነት ግን እመካለው

የከበደው ሸክሜ ይቀለኛል ይቅርታ ለባሪያህ ይደርሰኛል

በመቅደስህ ቆሜ ለመዘመር ስራህን ለትውልድ ለመመስከር

እኔ ማነኝ ብዬ አስባለው አምላክ ቸርነትክን አደንቃለው

...በሰው እጅ መመካት አቁሜያለው እረዳቴ አንተ ነህ አውቀዋለው

አንተ ከጠበከኝ በህይወቴ ቅጥሬ አይደፈርም መድሃኒቴ

የኔን ስራ ተወው ተግባሬን የመስቀሉን ነገር መርሳቴን

አዚሜን አንስተህ አንተን ልይህ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላኬ ነህ

7 አይሸሽግ እውነቱ

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

አይሸሽግ እውነቱ ማርያም ቅድስት ናት

ማርያም ብጽእት ናት

<u>ከእግዚአብሔር ያልተላከ አይቸልም ሊያወድሳት</u> (2)

...ገብርኤል ከከፍታ ከራማ ታላቅ ቤቱ

ገሊላ የተገኘው ወደ ማርያም እህቱ

ከእግዚአብሔር መላኩን ተረዳን በምስጢር

ለስሟ ክብርን ሰጥቶ ሰምተነዋል ሲያበስር

...በዘካሪያስ ቤት አቀረብሽ ምስጋና

የባሪያውን ውርደት ተመልክቷልና

ፍጥረት ብጽእት ካለሽ ሆኖ በእንድ ቃል

ላንቺ ያልዘመረ እንዴት ትውልድ ይባል

...ቢያከበርሽ ገብርኤል በታላቅ ትህትና

ልእልናሽ በልጦበት ከእርሱ ቅድስና

ከልቡ አመንጭቶ መች ሆነ ማክበሩ

እግዚአብሔር ልኮት ነው ላንቺ መዘመሩ

...አንዳች አይጎድልብኝ አንቺን አወድሼ

ዝማሬን ባበዛ ያለኝን ጨርሼ

እንኳን ለማርያም ለአዶናይ እናት

ምስጋናን ሰጥቷታል ለአቢጊያ ዳዊት

8 ከወገኔ ጋራ እዘምራለሁኝ

©ሊ/መ/ ይልማ ሃይሉ

ከወገኔ ጋራ እዘምራለሁኝ

በደስታ በሃሴት ስሙን ጠራለሁኝ

ምግብና መጠጤ አምላኬ ነውና (2)

ዘወትር አቀርባለው ለጌታ ምስጋና (2)

...ህዝቡ ተሰብስቦ በቤተክርስቲያን

ሲዘመር ደስ ይላል በአንድነት ሆነን

በረከት የሞላው ዝማሬ ይገርማል (2)

ከእጣኑ ጋራ ወደ ላይ ይወጣል (2)

...ቀሳውስቱ ሌሊት ማህሌት ሲያቀርቡ

ከመላእክቱ ጋር ወረብ ሲወርቡ

ብርሃንን ለብሰን በደስታ ስንዘምር (2)

ትዝታው ልዩ ነው ህሊናን ሲሰውር (2)

...እራእይ ነውና ኑና ተመልከቱ

ሰዎች ሲዘምሩ እንደ መላእክቱ

የጽጌው ማህሌት የትንሳኤው ደስታ (2)

ልዩ ዝማሬ ነው እንዳመስለን ተርታ (2)

❾የደማስቆ ምርኮኛ ነኝ

© ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

የደማስቆ ምርኮኛ ነኝ የተሸነፍኩ

ፍቅሩ ሰብሮ የጠገነኝ የተፈወስኩ

ማሳደጃ ደብዳቤን ከእጅ ጥሎ (2)

ዳሶን ሄደ በልቤ ላይ ወንጌል ተክሎ (2)

...ዛቻዬን አነሳ ከወንድሞቼ ላይ

ጉዞዬን ጀመርኩኝ በአዲሱ ምእራፍ ላይ

ሳኦል ከነ ስሜ ታሪኬ ታሪኬ ተዘግቷል

ስሙን ካመኑት ጋር ነፍሴ ተቀላቅሏል

...የፍቅሩ ብርሃን ደማስቆ የጣለኝ

ልቤን አሸንፎ ለአገልግሎት ለየኝ

የመውጊያውን ብረት ላልቃወም ከቶ

አስተምሮኝ ሄደ ፍቅሩ ልቤን መቶ

...ስሙን ያመኑትን ለመግደል ወጥቼ

ተሸንፌ መጣው እኔ ራሴ ሞቼ

ገዳይ ነው በፍቅሩ አይተውም አቁስሎ

ሞቴን ወሰደልኝ ህይወት በእጁ ጥሎ

...ለእኔ ሚረባኝን ስለ እርሱ ንቄያለው

ቢሆን በሞቱ እንኳን ልመስለው እወዳለው

ግደል ያላችሁኝ ስሙን ያመኑትን

ከሚገደሉት ዘንድ ፈልጉት ዳውሎስን

❶❿አለና ሚካኤል

© ሊ/መ/ ይልማ ሃይሉ

አለና ሚካኤል አምላኩን ማለደው

ዘወትር ስለ እኛ መለመን ስራው ነው

...ህጻናት በረሃብ ሲረግፉ አይቻለው

ስለዚህ አምላኬ ልማልድህ መጣው

ምድር ብረት ምጣድ ሆና ተቃጥላለች

እናት ለልጆቿ የምትሰጠው አጣች

...የሻገተ እንጀራ ፍርፋሪ ጠፋ

ምድር በውሃ ጥም በረሃብ ተቀሰፋ

ስለዚህ ታረቀው ይቅር በለው አለ

ሚካኤል በሰማይ ከአምላኩ ፊት ሳለ

...አይቼአለው አለ ሰባ አመት ሲቆጣ

የምህረት ፀሃይ በኢትዮጵያ ይምጣ

ሜዳው አረንጓዴ አበባ ይሞላ

ደመናው ይመለስ የምህረት ጥላ

...ሚካኤል አምላኩን ማለደው በብርቱ

ዳግም እንድታበቅል አዝርዕት መሬቱ

ጠላትም እንዲያፍር ህዝቡም እንዲጽናና

እግዚአብሔር በምህረት በረድኤትህ ና

❶❶ ትንሳኤሽን ያሳየን

© ሊ/መ/ ይልማ ሃይሉ

ትንሳኤሽን ያሳየን ያሳየን (2)

ውዲቷ ኢትዮጵያ ሃገረ እግዚአብሔር

ትንሳኤሽን ያሳየን

...የአባቶች ዘመን ተመልሶ እንድናይ

አለን ኢትዮጵያ ሆይ የፍቅር ራእይ

ትንሳኤሽን ያሳየን

ትቢያሽን አራግፈሽ ሃዘንሽን ሽረሽ

ዳግም ተነሺያለሽ ሃገሬ እንደ ድሮሽ

ትንሳኤሽን ያሳየን

...ያልታዘዘች ሃገር ለእግዚአብሔ ስርአት

አያጣትምና ዘወትር ፍርሃት

ትንሳኤሽን ያሳየን

ከቁጣው አምልጣ ሰላም እንድታገኝ

ሰው ሰው ህሊናው ይገናኝ

ትንሳኤሽን ሳየን

...ይቅርታ ታላቅ ነው ቁስልን ይሽረዋል

ጸብ ግን እስከ ዛሬ እነ ማንን ጠቅሟል

ትንሳኤሽን ያሳየን

ቂምና በቀል ለትውልድ ያቆዩ

በማይበርድ እሳት ውስጥ ህዝቡን ያጋያሉ

ትንሳኤሽን ያሳየን

❶❷ቸርነትህ ብዙ

©ዲ/ አሸናፊ ተሾመ

ቸርነትህ ብዙ ምህረትህ ብዙ

በጉዞአችን እርዳን ጠባብ ነው መንገዱ

ድንቅ ነው አምላክ ሆይ ፍቅርህ ለኛ

ድንቅ ነው ለኛ አንተ ነህ መልካም እረኛ

...እስራኤል ወደቀ እስራኤል ተነሳ (2)

መንገዱ አልቀናውም አምላኩን ሲረሳ (2)

የያዕቆብ አምላክ እግዚአብሔርን ይዞ (2)

ምን እንዳተረፈ አውቆታል በጉዞ (2)

...መንገዱ አይታከትም ጎዳናው የቀና (2)

እግዚአብሔር ከፊት ከውህላም አለና (2)

እርሱ የሌለበት ቢመችም መንገዱ (2)

አቅጣጫው ወደ ሞት አይቀርም መውሰዱ (2)

...በመንገዱ ዝለን ወድቀን መች ቀርተናል (2)

የያዕቆብ አምላክ ደግፎ አንስቶናል (2)

እግዚአብሔር ሲጠራን በቀደመው መንገድ (2)

ጉዞአችን ወዴት ነው በሞት ለመወሰድ (2)

...አምላክ ሆይ ፍቅርህን በልባችን ሳለው (2)

እስከሞት በመስቀል የወደደን ማነው (2)

በበረሃው ጽናት ሲጸናብ ረሃቡ (2)

በረከት ሞላኸው ተረፈልን ምግቡ (2)

❶❸ምስክርነቱን ገለጸ

©ዘማሪት አዳነች

ምስክርነቱን ገለጸ ቂርቆስ ህጻን (2)

በእሳት ተፈትኖ አለፈ ፈተናውን

በእሳት ተፈትኖ አለፈ ኧኸ ፈተናውን ደስ ይበለን

...ቂርቆስ ኢየሱጣ ሁለቱም በአንድ ልብ ምንኛ ጨከኑ (2)

ተቃቅፈው ሲገቡ ወደ እሳት ጋኑ (2)

...ህጻኑና እናቱ በእሳት ውስጥ ሲዋኙ ያለ ምንም ፍርሃት(2)

ገብርኤል ተላከ እነርሱን ለማውጣት (2)

...በርዶና ቀዝቅዞ የእሳቱ ነበልባል በጌታችን መስቀል

ሁለቱም ሰማእታት ተጎናጸፉ ድል(2)

❶❹በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

©ዘማሪት አዳነች

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

ተግባረ ተክለ አብ ብእሴ ማገስ (2)

ይነገር ይሰማ እስከ አጽናፍ ድረስ

የሚሆን ነውና ለህሙማን ፈውስ (2)

በቃልኪዳኑ አምነሽ በሰጠው ፈጣሪ

ለምግባረ ሰናይ ነፍሴ ተጣጣሪ (2)

...ጋሻ ጦር ይዞ ከማደን አራዊት

የሰው ልጅን ሊያድን ሥላሴ መረጡት (2)

አጋእዝተ ዓለም ጸጋን የሚሰጡ

ተ/ሃይማኖት ብለው ስሙንም ለወጡ(2)

...በክዴተ እግሩ ኢትዮጵያን ቀድሶ

ወጣ ደብረ አስቦ በሩጫ ገስግሶ(2)

እግሩ እንኳን ቢሰበር በመቆም ብዛት

ለሰባት አመታት ጸና በጸሎት(2)

❶❺ሰአሉ ለነ

©ዘማሪት አዳነች

ሰአሉ ለነ ቅዱሳን መላእክት (2)

ሰአሉ ለነ ጻድቃን ሰማእታት

ሃበ አምላከ ምህረት ሰአሉ ለነ

ለምኑልን ቅዱሳን መላእክት (2)

ለምኑልን ጻድቃን ሰማእታት

ወደ አምላከ ምህረት ለምኑልን

...የመረጥከውን ማን ይከሳል

ያስቀመጥከውን ማን ይወስዳል

ለሚገባው ክብርን መስጠት

ታጉርልና በመጻህፍት
<u>በህይወታቸው ያስደሰቱህን</u> (2)

<u>እናከብራለን ቅዱሳንህን</u> (2)

...ጽኑ መዳንን እንዲይዙ

የሚላኩ ሚታዘዙ

ሰርክ በፊትህ እየቆሙ

ጥዑም ቅዳሴን እያሰሙ

<u>በምስጋናቸው የሚያከብሩህን</u> (2)

<u>እናከብራለን መላእክትህን</u> (2)

...ጤዛ ልሰው ዳዋ ጥሰው

ዋኢይ ቁሩንም ታግሰው

በየፍርከርክታወ በየ ዱሩ

ሌጦ ለብሰው እየዞሩ

<u>በስርአታቸው ያከበሩህን</u> (2)

<u>እናከብራለን ጻድቃኖችህን</u> (2)



ከላይ የቀጠለ

...እንደ ሚታረዱ በጎች ሆነው

አንገታቸውን ለሰይፍ ሰጥተው

ስለስምህ እየተጠሉ

ከአንበሳ ጋር እየታገሉ

<u>በተጋዶሎአቸው ያከበሩህን</u> (2)

<u>እናከብራለን ሰማዕታትህን</u> (2)

...ከህያው ቃልህ እየጠቀሱ

መናፍቃንን ድል የነሱ

በገዛ ደምህ የዋጀሃትን

ቤተክርስቲያንን የጠበቋትን

<u>ያከበርካቸው ባሪያዎችህን</u> (2)

<u>እናከብራለን ሐዋርያትህን</u> (2)

❶❻አንቺን የያዘ ሰው

©ዘማሪት ጸዳለ ጎበዜ

አንችን የያዘ ሰው ምን ይጎድልበታል

በምልጃሽ በረከት ቤቱ ሞልቶለታል

ዘር መከር ባይኖረው ጎተራው ባይሞላ

ሁሉም ይሸፈናል በረድኤትሽ ጥላ (2)

...በረከትሽ ብዙ የደናግል ገንዘብ

የምስኪናን እናት የርሁባን ቀለብ

ለሁሉ መጋቢ ጸጋሽ የማይጎድል

ስምሽ ጥሉም ምግብ ከረሃብ የሚያስጥል (2)

...አንቺ ብትመጪ ከምስኪኗ ቤቴ

እንደ መጥምቁ እናት በዛልኝ ሃሴቴ

የአዲስ ኪዳን ቁርባን መንበር ጠረጴዛ

ጽድቅን አሸተትሽን የህይወትሽን መአዛ

...ልቤ ተጠራጥሮ ኪዳንሽን ካለረከዳ

ልመናም አልወርድም አልይዝም አቆፋዳ

ሁሉን እየሞላሽ መመገብ ታቂያለሽ

ቢዝቁት የማያልቅ ጸጋና ሃብት አለሽ

...የእግዚአብሔር ማረፊያ ኮሬባዊት ዋሻ

የህይወት ውሃ ምንጭ የህግ መፍሰሻ

ነበልባል ተዋህዶሽ ሙሴ አንቺን አይቷል

ጫማውን አውልቆ በፊትሽ ተደፍቷል

❶❼ቅዱስ ሚካኤል

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

ቅዱስ ሚካኤል (3) ነፍሴ ሲጨነቅ ሲዝል ሲጋዬ

ፈጥነህ ተራዳኝ ዋስ ጠበቃዬ

...አንተ ስለሆንክ ሚካኤል

የአምላክ ባለሟል "

ልመናህ ፈጥኖ "

ከአምላክ ይቀርባል "

የዋህ መልአክ ነህ አዛኝ ለሰው (2)

ምልጃህ ፈጣን ነው ለምናምነው (2)

...ደዌ የጸናበት ሚካኤል

ባንተ ይድናል "

በአደባባይ "

ምስክር ሆኗል "

ከቤትህ መጥቶ የተማጸነ (2)

በቃል ኪዳንህ ህይወቱ ዳነ (2)

...ከአምላክ ተሰጥቶህ ሚካኤል

ክብርህ ያበራል "

ለጎስቋላው ሰው "

መጠጊያ ሆኗል "

ትልቅ ትንሹ ደሃው ሃብታሙ (2)

ለምኖ አግኝቷል ከአምላክ በስሙ (2)

...በብሉይ ኪዳን ሚካኤል

ከአምላክ ተልከህ "

ህዝበ እስራኤልን "



ከላይ የቀጠለ

በሐዲስ ኪዳንም ድንቅ ስራ አለህ (2)

በተአምራትህ ትፈውሳለህ (2)

...ባለ መድሃኒት ሚካኤል

ያቃተውን "

ፈዋሽ ጸበልህ "

ሆኖኛል ሃይል "

እንደ መጻጉዕ ድህነት አገኘው (2)

ፈውሰኸኛል በአንተ ተመካው (2)

❶❽እግዚአብሔር ጠራሁት

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

እግዚአብሔር ጠራሁት በሃዘኔ ጊዜ (2)

አወጣኝ ከጭንቀት ከሃዘን ከትካዜ (2)

...የልመናዬን ድምጽ እርሱ ሰምቷልና

ጆሮውን ወደ እኔ አዘንብኳልና

በዘመኔ ሁሉ ስጠራው እኖራለው (2)

ጎስቋላ ብሆንም ምስጋና ዘቀርባለው (2)

...እንደ ቃልህ መሄድ መራመድ አቅቶኝ

የሃጢአቱ መንገድ ማዕበሉ ገፍቶኝ

ወደ እርሱ ስማጸን ደግሞ ስጸጸት (2)

አላሳፈረኝም መጣ በምህረት (2)

...ኖህን እንዳደንከው እኛንም አድነን

ከቀስቱ እንድናመልጥ ምልክት ስጠን

በትርህ ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኝ (2)

አንተ ከእኔ ጋር ነህ አልፈራም ክፉውን (2)

...በበዛው ምህረቱ ያለፈውን ትቶ

በፍቅሩ ጎበኘኝ አልተወኝም ከቶ

ሊቀበለኝ ወዶ ፊቱን አበራልኝ (2)

ማን ይቃወመኛል እግዚአብሔር ካለልኝ (2)

❶❾እልል በሉ

©ዘማሪ ፍቃዱ አማረ

እልል በሉ በአንድነት ዘምሩ

አመስግኑ ለከብሩ ዘምሩለት

እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም በሉ

...በኃጢአት ባርነት ስንኖር ተገዝተን

ከቤቱ ስንርቅ ትእዛዙን አፍርሰን

አይቶ ዝም ላለን ጠላቶቹ ሳለን

ውለታው ብዙ ነው ክብር ለእርሱ ይሁን (2)

...ራሱን አዋርዶ እኛን አከበረን

ሲጋውና ደሙን ብሎ ጠጡ አለን

መልካም እረኛ ነው የሚያሳጣኝ የለም

ምስጋና ይድረሰው ለመድኃኒአለም (2)

...ህይወቱን የሰዋ እንደ አምላክ ማን አለ

ለሰው ልጆች ብሎ በመስቀል የዋለ

ፍቅሩ የማይለካ አያልቅም ቢወራ

ከሰማያት ወርዶ ሆነ ከእኛ ጋራ (2)

...ስራውን እናድንቅ እንዲህ ለወደደን

ከማያልቀው ፍቅሩ በረከት ላደለን

ለማይነገረው ለአምላክ ስጦታ

ውዳሴን እናቅርብ እንዘምር በእልልታ (2)

❷❶ባክኛለውና

©ዲ/ ወንደወሰን በቀለ

ባክኛለውና በስጋ ፈተና

የዚህ ዓለም ሃዘን ጫፍ የለውምና

ፈጥነሽ ወደኔ ነይ ከትንሿ ቤቴ

አጽናኚኝ እመ አምላክ ድንግል እመቤቴ

...ባህሩ ትልቅ ነው ድንግል እመቤቴ

ትንሽ ናት መርከቤ (2) "

የመንገዴ መሪ "

አንቺ ነሽ ወደቤ (2) "

...በመንገዴ ብዝል ድንግል እመቤቴ

አለም ትሰቃለች (2) "

መመኪያ ርስቱ "

ወዴት ነች እያለች (2) "

...በቀቢጸ ተስፋ ድንግል እመቤቴ

እንዳልወድቅብሽ (2) "

በቀንም በሌሊት "

ተስፋዬ አንቺ ነሽ (2) "

...የለም ያተረፍኩት ድንግል እመቤቴ

ወጥቼ ወርጄ (2) "

ትርፌ አንቺ ብቻ ነሽ "

ፅዮን አማላጇ (2) "

❷❶ልቤ በእግዚአብሔር ጸና

©ዲ/ ወንድወሰን በቀለ

ልቤ በእግዚአብሔር ጸና (2)

አፌን አላቀኩኝ ለስሙ ምስጋና

...በጠላቶቼ ላይ አፌ ተከፈተ

ማዳኑን አይቼ ልቤ ተደሰተ

እንደ እግዚአብሔር ያለ እረዳት ማን አለ

ደካማ ባሪያውን ስለተቀበለ

...ጠግበው የነበሩ እንጀራን ተራቡ

ተርበው የነበሩ እረኩ ጠገቡ

መች ጎድሎብኝ ያውቃል አንተን ተደግፌ

በእጆችህ በረከት ተሞልቷል መዳፌ

...እግዚአብሔር ይገድላል እንዲሁም ያድናል

የሃይለኞችን ክንድ ሰብሮ ይታደጋል

መካኒቱ ሐና ወለደች ሰባት

ስራህ ይደንቀኛል በቀን በሌሊት

...ምስኪኑን ከጉድፍ ያነሳል ከምድር

ይዘረጋለታል የክብሩን ወንበር

ተመከረ ልቤ ሐናን ተመልክቶ

እግዚአብሔር ለጋስ ነው ለጠበቀው ተግቶ

❷❷ስለማይነገር ስጦታው

©ዘማሪ ቸርነት ሰናይ

ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

ቸል ያላለን አምላክ ስንጓዝ ማዕበሉን አቋርጠን

ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

...የህይወት እስትንፋስ ዘራብን ህያው እንድንሆን

ይህን ያደረገ አምላካችን እግዚአብሔር ይመስገን

ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

...ነፋሱን ገስጾ ማዕበል አቁሞ የሚያሻግር

የዓለም ፈተና ቢበዛ እርሱ መጠጊያችን

ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

...ዳግም እንዳንሞት በሞቱ ሞትን የረታልን

የምንመካበት ትንሳኤን ሰላምን ለሰጠን

ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

...ከሲኦል እስራት ተፈተን ነጻ የወጣንበት

መስቀሉን ለሰጠን ለአምላካችን እንዘምር በእውነት

ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

❷❸ ጥሪህም ድንቅ ነው

©ዘማሪ ወንድወሰን ዓለሙ

ጥሪህም ድንቅ ነው ዮሴፍ መመረጥህ ልዩ (2)

ምልክቶች ሁሉ ክብርህን አሳዩ

...ጻዲቁ አባታችን ቅዱስ ዮሴፍ

አምላክን ይዘሃል ስደት ላይ በእቅፍ

እኔንም ደግፈኝ በእነዚያ እጆችህ

ዘውትር እንዲገለጥ ጽድቅና ክብርህ

...ከቤተመቅደሱ አይሁድ ሲያስወጧት

እንደምን ላድርግሽ አካሪያስ አላት

አመልክት አለችው ወደ አምላካችን

እርሱ ያመልክትህ ጠባቂ የኔን

...የካህኑ ጸሎት አርጎ ወደ ላይ

በትርህ አፍርቶ ምርጫህንም ሲያሳይ

ርግብም ወረደች ከታላቁ ሰማይ

ብኪልና ጌታ የእናቴ አገልጋይ

...በዚያ በግብጽ ሃገር በታላቅ በረሃ

ታምነህ አገለገልክ እየለመንክ ውሃ

ዛሬም ተንበርክኬ ደክሜያለው ስልህ

ለምንልኝ የሴፍ አማልደኝ ከአምላክህ

❷❹ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን

©ዘማሪ ፍቃዱ አማረ እና ዘማሪት አዜብ

ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን (2)

ለታላቁ ክብር ለዚ ላበቃን ከሞት ወደ ህይወት ላሸጋገረን

ኑ በእግዚአብሔር ኑ በድንግል ደስ ይበለን (2)

...የሰማዩን መንግስት እርስቱን ለሰጠን

ከጨለማ አውጥቶ ብርሃንን ላሳየን

ለዚህ ድንቅ ውለታው ምስጋና ያንሰዋል

በእርሱ ደስ ይበለን ክብር የገባዋል

...ከዓለት የፈለቀ ውሃ ጠጥተናል

ሰማያዊ መና አምላክ መግቦናል

ፍቅርህ የበዛ ነው ምን ልክፈልህ ጌታ

ስምህን ላመስግነው ከጧት እስከ ማታ

...በቃዴስ በረሃ ምንም በሌለበት

በኤርትራ ባህር ወጀብ በበዛበት

ለእርሱ መንገድ አለው ከቶ ምን ተስኖት

ልባችሁ አይፍራ በፍጹም እመኑት

...በባርነት ሳለን በድቅድቅ ዓለም

ብርሃንን አገኘን በድንግል ማርያም

ያጣነውን ሰላም ዛሬ አገኘን

እጅግ ደስ ይበለን በእመቤታችን

...የሐና የኢያቄም የእምነታቸው ፍሬ

በእግዚአብሔር ፈቃድ ተወለደች ዛሬ

የኢያቄም ስእለቱ የሐና እምነ

ለምኝልን ለኛ ኪዳነምህረት

❷❺ኪዳነ ምህረት

©ዘማሪት ለምለም ከበደ

ኪዳነ ምህረት እመቤት (2)

ነይልን ነይልን ካለንበት

...ከሰማያት በላይ ካለው በማደሪያሽ (2)

ዝማሬ ከሞላው ከዘላለም ቤትሽ

የምድር ፍጥረታት ማርያም ማርያም ሲሉሽ (2)

የቃል እናት እመቤቴ ነይ በሰረገላሽ (2)

...ከጸጥታ ወደብ ከፍቅር አውድማ (2)

ከሰላሙ መንደር ከእውነት ከተማ

ሰዓሊ ለነ ቅድሰት ውዳሴ ሲሰማ (2)

ከሚካኤል ከገብርኤል ጋር ነዪልን ከራማ (2)

...ዘርፋፋው ቀሚስሽ ይውረድ ከሰማያት (2)

እንባችን ይታበስ በአንቺ አማላጅነት

የጽዮን ዝማሬ ተሞላ ነፍሳችን (2)

ነዪ(3) እንበል እንዳባቶቻችን (2)

...ፍጥረታት ሊድኑ በአማላጅነትሽ (2)

የዘላለም ኪዳን አማኑኤል ሰጠሽ

ትውልድ ይህን አምኖ ብጽእት ይሉሻል (2)

እናቴ መመኪያዬ ምርኩዜ ሆነሻል (2)

...የልብን ሲያዋዩሽ ሰምተሽ ዝም አትዪም (2)

ችግረኛን አይቶ ልብሽ አይጨክንም

ከዓይን ጥቀሻ ፈጥነሽ ትደርሺለታለሽ (2)

ከሐዘን ከመከራ ታሳርፊዋለሽ (2)

❷❻እውነተኛ ሰላም

©ዘማሪት ለምለም ከበደ

እውነተኛው ሰላም ያለው ከቤትህ ነው (2)

እርዳኝ አልናወጽ እለምንሃለው (2)

...ታጢአቴን ሳስበው ልቤ ይጨነቃል

ካንተ መለየቴ ነፍሴን አድክሚታል

ወዳንተ መልሰኝ እኔ እመለሳለው

እውነተኛው ሰላም ያለው ከቤተህ ነው

...በቅዳሴው ጸሎት ዘውትር እንዳልተጋው

በአደባባይ ቆሜ ስምክን እንዳልጠራው

ተሰነካክዬ ወድቄያለውና

እርዳኝ አማኑኤል በሃማኖት ልጽና

...ዓይኔም እንባን ያምንጭ ያልቅስ ስለ ሃጢአቴ

የንስሃ ትሁን ቀሪዋ ህይወቴ

በመዳኔ ሰአት በዛሬዋ እለት

ፍቅርህን አስቤ መጣው ካንተ ቤት

...ጌታ ሆይ ጸጸቴን እንባዬን ተቀበል

አባትሽ ነኝ በለኝ እኔም ልጅ ነኝ ልበል

ዘይት ሳላዘጋጅ ድንገት መጥተህብኝ

በርህን በመዝጋት ከደጅ አታስቀረኝ

❷❼ አቡነ አረጋዊ

©ዘማሪት ለምለም ከበደ

አቡነ አረጋዊ ጻዲቁ መነኩሴ

በኃጢአት እንዳትሞት ህያዊቷ ነፍሴ

ጻዲቁ አማልደኝ በቅድመ ሥላሴ (2)

...ከእናት ከአባት ፍቅር አቡነ አረጋዊ

አምላክን መርጠሃል "

መከራ መስቀልን በእውነት ታግሰሃል

የእግዚአብሔር ቸርነት ከሞት ሰውሮሃል

...ምስጢረ መለኮት አቡነ አረጋዊ

በልብህ ቢሞላ "

አረጋዊ ተባልክ ሳለህ ህጻን ጨቅላ

ጸጋህ ትደርብን ትሁንልን ጽላ

...ከዳሞት ተራራ አቡነ አረጋዊ

ከማኅሌት ከተማ "

የፅዮን ዝማሬ ነፍስህ ብትጠማ

በዘንዶ ተጉዘህ ሰማህ ያንን ዜማ

...የህግ መምህር አቡነ አረጋዊ

በረከት አድለን "

ወደ ሃይል በእምነት አሻግረን

ወደ ጌታ ደስታ በምልጃህ አቅርበን

❷❽እግዚአብሔርን አመስግኑ

©ዘማርያን አረጋይ ገ/መድኅን እና ጸዳለ ኀበዜ

እግዚአብሔርን አመስግኑት

ስራህ ግሩም ድንቅ ነው በሉት (2)

...ሰማይን ያለ ማሰሶ ምድርንም ያለ መሰረት

ያጸናው እርሱ ነው ስራህ ድንቅ ነው በሉት

...የባህርን ጥልቀት የመጠነ ዳርቻዋን የወሰነ

እግዚአብሔርን አመስግኑት ስራህ ግሩም ድንቅ ነው በሉት

...ማዕበል ነፋሱን የሚገስጽ ፍጥረቱ ለስሙ የሚታዘዝ

ትጉህ እረኛ ድካም የሌለበት እግዚአብሔርን ስራህ ድንቅ ነው በሉት

...ንጹህ ባህርይ ነው ሁሉን የሚገዛ የነገስታት ንጉስ አልፋና ኦሜጋ

ዘላለም እርሱ የማይለወጥ እግዚአብሔርን ስራህ ድንቅ ነው በሉት

...ጥበብን የሚሰጥ ጥበበኛ ፍርድ የሚያደርግ እውነተኛ ዳኛ

እንደ እርሱ ያለ ከቶ አይገኝም እግዚአብሄር ግሩም ነው ዘላለም

❷❾በምን በምን እንመስላት

©ዘማሪያን አዲስ ለማ፡ ጥላዬነሽ፡ ወርቅነሽ ተፈራ

በምን በምን እንመስላት ድንግል ማርያምን (2)

ምሳሌ የላትም የላትም ክብሯን የሚመጥን (2)

...የሙሴ ጽላት ነች የምህረት ቃልኪዳን

የያዕቆብ መሰላል የአብርሃም ድንኳን

የብርሃን መውጫ የኖህ ድንቅ መርከብ

የመላእክት እህት የሩህሩሃን ርግብ (2)

...የሰሎሞን አክሊል የአሮን በትር

የእዝራ መሰንቆ የጌዲዮን ጸምር

ድንግል እመቤት ናት የጻድቃኖች በር

ሆና የተገኘች የአምላክ ማህደር (2)

...የቅዱሳን እናት የአለም ንግስት

ችላ ተሸከመች መለኮተ እሳት

ብርሃን ትሁነን ጨለማን ገላልጣ

አማልዳ ታስምረን ከዚህ ዓለም ጣጣ (2)

...ከማር ይጣፍጣል የድንግል መአዛ

አምላክን አቅፋለች በሁለት እጇ ይዛ

ዓለም ሁሉ የዳነው በልጅሽ ነውና

እናታችን ጽዮን ይድረስሽ ምስጋና (2)

❸❼ ነዪ ነዪ

©መ/ቀ/ ዘበነ ለማ

ነዪ ነዪ ማርያም ነዪ ነዪ

ድንግል ሆይ ነዪ ነዪ

ያን የእሳት ባህር ከቶ እንዳላይ

...በሐመረ ኖህ የተመሰልሽ

በአሮን በትር የተመሰልሽ

<u>የምስራቋ በር</u> (2) ቶሎ ድረሽ

...በተራራማው በኤፍሬም ሃገር

እንግዳ የሆንሽ ለኤልሳቤጥ በክብር

<u>ነዪልኝ ወደኔ</u> (2) ካንቺ ጋር ልኑር

...ዓለም ከብዶብኝ ተጨንቄያለው

ሃዘን በዝቶብኝ ብቸኛ ሆኛለው

<u>ኧረ ነይ ድንግል ሆይ</u> (2) እጠራሻለው

...ጥበቡ አንቺ ነሽ ለሲሎንዲስ

ነይ ብሎ ሚጠራሽ ሱላማቲስ

<u>አትጥፊ ድንግል ሆይ</u> (2) ደጅሽ ስንደርስ

...ምስጥር የገለጥሽ ለሕርያቆስ

ፈጥነሽ ያማለድሽ በቤተ ዶኪማስ

<u>ነዪልኝ እናቴ</u> (2) ልቤ ይፈወስ

...ድንግል ቀርባለች ጪኧቴን ሰምታ

የኃጢያቴ ገመድ እስሩ ተፈታ

<u>አከብርታለው</u> (2) ልጇ በእልልታ

❸❶ለማርያም

©ማኅበረ ሥላሴ

ለማርያም (2)

እንዘምራለን ለዘላለም (2)

...የተዘጋች ደጅ ለዘላለም

ህዝቅኤል ብኪል "

ንጽህይት ናት በእውነት "

በፍጹም ድንግል "

አብነት አርገን "

እኛም እርሱን "

በፍጹም ፍቅር እንዘምራለን (2)

...የዋህት ርግብ ለዘላለም

ሰላም አብሳሪ "

ለጨለማ ህይወቴ "

ብርሃንን አብሪ "

እማጸንሻለው "

ድንግል ለነፍሴ "

አደራ ቅድስት አንቺ ነሽዋሴ (2)

...እጅግ የበዛ ነው ለዘላለም

ያለኝ ፍቅር "

አይወሰንም "

አይነገርም "

በእርሷ ደስ ይለኛል "

ሐሴት አደርጋለው "

ስሚን እየጠራው እዘምራለው (2)



ከላይ የቀጠለ

...ነዪ ነዪ ስላት ለዘላለም

ቀን እና ሌሊት ″

አትለየኝም ″

ለእኔስ ቅርቤ ናት ″

እጹብ እጹብ ብለው ″

አመሰገኗት ″

<u>ክብሯን ሊገልጹ ቢያጥራቸው ቃላት</u> (2)

❸❷በሐዘኔ ደራሽ ነሽ

©ዘማሪ ዋኘባቸው

በሐዘኔ ደራሽ ነሽ በጭንቀቴ

ለችግሬም ደራሽ ነሽ

የአምላኬ እናት ጌታዬ እናት

ድንግል እመቤቴ ወላዲተ ቃል

...መልካሚቷ ርግብ ድንግል እመቤቴ

ማርያም እናቴ ነሽ "

ከፍጥረታት ሁሉ "

ገናና ነው ክብርሽ "

የሐዘኔ መጽናኛ "

እንባዬን አባሽ ነሽ "

...ዋሻ መጠለያ ድንግል እመቤቴ

የዘላለም ቤቴ "

መንገድ ስሄድ ስንቄ "

መጠጌ ነሽ ምግቤ "

እመ አምላክ ስጠራሽ "

ይጠፋል ረሀቤ "

...የእናትነትሽን ድንግል እመቤቴ

ፍቅርሽን አየሁኝ "

ጎጆዬን ስትሞዪው "

ባዶ የሆነውን "

አንቺ እያለሽልኝ "

ምን እሆናለሁኝ "

❸❸የሥላሴን መንበር

©ዘማሪት ብቻዬ

የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት

ኪሩቤል በደመና ዙፋኑን ይዘውት

ድንግልን ከመሀል ሚካኤልን ከፊት

አእላፍ መላእክት ሲሰግዱ በፍርሃት

እዩት ተመልከቱት የሰማዩን ድምቀት

እዩት ተመልከቱት የሰማዩን አባት

...የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት

እያሸበሸቡ የሰማይ መላእክት

ካህናተ ሰማይ ሥሉስ ቅዱስ ቅዱስ ሲሉት

ይህን ታላቅ ክብር ሊያዩ የታደሉ

በጽድቅ ስራቸው በምድር ይታያሉ (2)

...የቅዱሳን ህብረት የቅዱሳን ሃገር

ሲያወደስ ይኖራል የሥላሴን መንበር

ጽድቅና ርህራሄ የተሞላ ሰማይ

እግዚአብሔር ያድለን በትንሳኤ እንድናይ (3)

❸❹ትህትናሽ ገሩም ነው

©ዘማሪት ብቻዬ

ትህትናሽ ግሩም ነው ደግነትሽም (2)

እናቱ ሆነሻል ለመድኃኔአለም (2)

...ንጽህይት ስለሆንሽ እመቤቴ እመቤቴ

እንከን ሌለብሽ "

ፍጽረታት ጌታ "

በአንቺ አደረብሽ "

የድንግል መመረጥ "

ዜናው አስገረመኝ "

እሳቱን ታቀፈች "

የማይቻለውን "

...ምርኩዜ ልበልሽ እመቤቴ እመቤቴ

ጥላ ከለላዬ "

ጋሻዬ ነሽ አንቺ "

ለእኔስ መመኪያዬ "

በአለም እንዳልጠፋ "

ህይወቴ መሮብኝ "

እንደ ወይን አጣፍጪው "

ድንግል ድረሺልኝ "

...የምስራቅ ደጃፍ ነሽ እመቤቴ እመቤቴ

የሁላችን ተስፋ "

እሙ ለፀሃይ ጽድቅ "

የሁሉ ጠበቃ "



ከላይ የቀጠለ

ድንግል የድል አክሊል "

ድንግል የጽድቅ ስራ "

ድንግል መስላል ነሽ "

ለተዋህዶ ተስፋ "

❸❺እመ ብርሃን

©ዲ/ ብርሃኑ እሸቱ

እመ ብርሃን መመኪያችን ነሽ (2)

የአዳም ተስፋ አለኝታችን ነሽ

እመ ብርሃን መመኪያችን ነሽ

...እመ ብርሃን የኣባቶቻችን

" ቃና ለዛቸው

" በችግር ጊዜ

" መንገድ መሪያቸው

" ምን ብዬ ልጠጥራሽ

" ላወድስሽ

" የምግባር ደሃ

" ባዶ ልጅሽ

...እመ ብርሃን የቅዱሳኑ

" ጣዕመ ዜማቸው

" አንቺ ነሽና

" ውብ ድርሰታቸው

" የእኛ ስጦታ

" የድል አክሊል ነሽ

" በአማላጅነትሽ

" ለታመኑብሽ

...እመ ብርሃን የይስሐቅ መአዛ

" ከፍኖተ ሎዛ

" የያዕቆብ መሰላል



ከላይ የቀጠለ

" የአቤል የዋህት

" የሴት ቸርነት

" የኢያሱ ሐውልት

" የህይወት ውሃ

" የሳሙኤል ዘይት

" ርግብ ሰናይ

" ንግስተ ሰማይ

...እመ ብርሃን መልካሚ ርግብ

" የኖህ መልእክተኛ

" የታጥአን ተስፋ

" የልብ ብርታቱ

" ምስራቻችን

" ውስጣችን ያለሽ

" በምድር በሰማይ

" አምሳያ የለሽ

❸❻ያሬድ ካህኑ

©ዘማሪ ብዙአየው ተመስገን

ያሬድ ካህኑ ዘመረ (2)

ዘመረ ያሬድ አምላኩን አመሰገነ

...አርያም በማለት ያሬድ ዘመረ

ማኅሌት ጀመረ " "

ዜማውን ከምልክት እያስተባበረ

ምስጋና አቀረበ ያሬድ ዘመረ

በዜማ መሳሪያ " "

ጽናጽንል አነሳ ከበሮ መቋሚያ

...በግዕዝ በዕዝል ያሬድ ዘመረ

በአራራይ ዜማ " "

ከብሉይ ከሃዲስ ምስጢር እያስማማ

በዜማው ምልክት ያሬድ ዘመረ

የአምላክን መከራ " "

የመስቀሉን ነገር የማዳኑን ስራ

...ደሙ እየፈሰሰ ያሬድ ዘመረ

በጦር ተወግቶ " "

ሊቁ ማኅሌታይ በመንፈስ ተቃኝቶ

በጥዕም ልሳኑ ያሬድ ዘመረ

በተሰጠው ጸጋ " "

ለንጉስ እግዚአብሔር ለአልፋ ኦሜጋ

ድጓ ጾመ ድጓ ያሬድ ዘመረ

ምዕራፍ መዋስዕት " "

ምስጢር ተገልጾለት ከሰማይ መላእክት

የዜማ መሰረት " "

ፈልፈለ ዝመሬ " "

የኢትዮጵ ያ ኩራት የተዋህዶ ፍሬ

❸❼ ውዳሴ ማርያም

©ሊ/መ/ቀ/እንግዳወርቅ በቀለ

ውዳሴ ማርያም እጮሃለው

ድንግል እናቴን እጣራለው

እንደ አባ ኤፍሬም ነይ ባርኪኝ

ወድሰኒ ልጇ በዪኝ

ውዳሴ ማርም በሰርክ ጸሎት ላይ

" ዜማ ስናደርስ

" ድንግል ትመጣለች

" ከቤተ መቅደስ

" የብርሃን ምንጣፍ

" ከፊቷ ተነጥፏል

" ቅዱስ ኤፍሬም ታጥቆ

" ያመሰግናታል

...ውዳሴ ማርያም አባ ሕርያቆስ

" ምስጋና ያቀርባል

" የቅዳሴው ዜማ

" ልብን ይመስጣል

" በጎ ነገር ልቤ

" አወጣ እያለ

" ዳዊት በገናውን

" እየደረደረ

...ውዳሴ ማርም ለንጽህናችን

" መሰረት ነሽና

" አንቺን ለማመስገን



ከላይ የቀጠለ

" ልቦናዬ ይብራ

" ተፈሰሐ ድንግል

" ኦ ቤተልሔም

" ካንቺ ተወለደ

" መድኃኔአለም

...ውዳሴ ማርያም ቅዱሳኑ ሁሉ

" ዙሪያሽን ከዋል

" አባ ጊዮረጊስም

" ንዒ ድንግል ይላል

" በወርቅ ዙፋን ላይ

" ተቀምጠሽ ሳይሽ

" ልቤ ተሰወረ

" ድንግል በግርማሽ

❸❽ጎሳ ልብየ

©ሊ/መ/ቀ/ እንግዳወርቅ በቀለ

ጎሳ ልብየ ቃለ ሰናይ (2)

ወአነ አየድእ ቅዳሴሃ ለማርያም (2)

...እኒስ የማርያምን ውዳሴዋን እናገራለው

እንደ አባቴ ዳዊት በበገና እዘምራለው

ቀን ከሌሊት ሳልል ለምስጋና እተጋለሁ

የጎጢአቴ ቁስል እንዲፈወስ እጮሃለሁ

ምርኩዜ ነሽና እመቤቴ በአንቺ እመካለሁ

...አ እመቤቴ በእውነት እንወድሻለን

እውነተኛ መብል ክርስቶስን ወለድሽልን

ምክንያተ ድኅነ ድንግል ማርያም የአምላክ መገኛ

በአማላጅነትሽ በመታመን እንጮህለን እኛ

ምህረትን አድይን ኪዳነ ምህረት የአለም መዳኛ

...ስለ ቸርነትሽ እመቤቴ ለእኔ እናቴ ነሽ

ስለ ንግስትነትሽም እመቤቴ ነሽ

ዝናባት ሳያጠጡት አየራትም ሳያሳድጉት

ሰማያዊ እነጅራ የሰጠሽን ቤቴልሔማዊት

ቅድስተ ቅዱሳን የኖህ መርከብ የአምላክ እናት

...ቃና ዘገሊላ በሰርጉ ቤት በዚያ ተገኝተሽ ሳለሽ

ውሃውን ወደ ወይን በአንቺ ምልጃ እንዳስለወጥሽ

ዛሬም የኔ ህይወት ባዶ ሆኖ ወይኑ አልልና

አንቺ የአምላክ እናት ንጽህይት ቅድስት ርህሪተ ህሊና

ህይወቴን አድሰሽ ቀድሰሽው ሙዪው በምስጋና

❸❾አስታርቂኝ

©ሊ/መ/ቀ እንግዳወርቅ በቀለ

<u>አስታርቂኝ ድንግል ማርያም</u> (2)

<u>ከልጅሽ</u> (2) ከመድኃኔአለም

...አስታርቂኝ ኃጢአትን ሰርቼ

" ጫካ ውስጥ ቆሜያለው

" ሰራዬ አሳፍሮኝ

" ዘውትር አነባለው

" ልጄ አዳም ብሎ

" አምላኬ ሲጣራ

" እነሆኝ ለማለት

" አንደበቴ ፈራ

...አስታርቂኝ ሃብትን ተካፍዬ

" ከገዛ አባቴ

" ከቤቴ ተሰደድኩ

" ይሻለኛል ብዬ

" ገፍቼ ወጥቼ

" የቤቴን ገበታ

" ልበላ ተመኘው

" የእንስሳት ገፈራ

...አስታርቂኝ ወደ አባቴ ልሂድ

" አሁን ተነስቼ

" ይቅርታ ልጠይቅ

" እግሩ ስር ወድቄ



ከላይ የቀጠለ

" ልጅነቴ ቀርቶ

" አድርገኝ ባሪያህ

" ከሙያተኞችህ

" እንደ አንዱ ቆትረህ

አስታርቂኝ ገና እሩቅ ሳለው

" አባቴ ኢይቶኝ

" ወደ እኔ እሮጦ

" አቅፎ ነው የሳመኝ

" ጠፍቶ የነበረ

" ተገኘልኝ አለ

" ሞቶ የነበረ

" ዳግም ህያው ሆነ

❹❶ ሀያል ሀያል

©ሊ/መ/ቀ/ እንግዳወርቅ በቀለ

ሀያል ሀያል (4)

ሰዳዴ ሳጥናኤል

ሀያል ገባሪ ሃይል

...ባሕራንን ያዳነው ተላፊኖስን የረዳው (2)

መልአኩ ሚካኤል ነው (2) የሞቱን ደብዳቤ የለወጠው

...ከእደ እረበናት (4) ሶስናን ያዳናት (2)

ሚካኤል መልአከ ምህረት

...ዲያቢሎስን ያዋረድከው በእሰት ሰይፍ የቀጣኸው (2)

ሚዛንህ ትክክል ነው (2) ሚካኤል ግብርህ ድንቅ ነው

...በሃዘን በትካዜ ያለሁትን ብላቴና (2)

አጽናናኝ አረጋጋኝ (2) ሚካኤል ሊቀ ደብረ ሲና

❹❶ለምኚ

© ሊ/መ/ቀ ምንዳዬ ብርሃኑ

ለምኚ ድንግል ለምኚ (2)

ለኃጥአን (3) አኮ ለጻድቃን

...ለምኚ ታላቅ ስጦታዬ

" አዛኝ ሩህሩህ ነሽ

" የጌታዬ እናት

" ጸጋን የተሞላሽ

" የአምላክ ማደሪያ

" ለምነሽ አስምሪኝ

" አማናዊት ጽዮን

ከእኔ አትለዪኝ

...ለምኚ ሐዘንሽ ሐዘኔ

" ለኔ ይሁን ድንግል

" የተንከራተትሽው

" በሃገረ እስራኤል

" ትዕግስትሽን ሳየው

" ልቤ ይመሰጣል

" የሐዘን እንባ ጎርፍ

" ዓይኔን ይላዋል

...ለምኚ በቀራንዮ አንባ

" በዚያ የፍቅር ቦታ

" በእግረ መስቀሉ ስር

" ከክርስቶስ ጌታ



ከላይ የቀጠለ

" ለእኛ ተሰጥተሸል

" እናት እንድትሆኚ

" ልጆችሽ ነንና

" ምልጃሽ ኣይለየን

ለምኚ እንደበቴን ጌታ

" በምስጋና ሙላው

" ደስ ይበልሽ ብዬ

" እኔም ላመስግናት

" አንደቤቴን ጌታ

" በምስጋና ሙላው

" ደስ ይበልሽ ብዬ

" እኔም ላመስገግናት

❹❷ አዘክሪ ድንግል

©ሊ/መ/ቀ እንግዳወርቅ በቀለ

አዘክሪ ድንግል (2) ለልጅሽ አሳስቢ አዘክሪ

ለኃጥአን አኮ ለጻድቃን

...ካንቺ መወለዱን አዘክሪ

በቤተልሔም "

በጨርቅ መጠቅለሉን "

መኾታው ግርግም "

...በዚያ በብርድ ወራት አዘክሪ

የገበሩለትን "

የአድግና የለም "

እስትፋሻቸውን "

...በግብጽ በረሀ አዘክሪ

መሰደድሽን "

የአሸዋው ግለቱን "

ረሀብና ጥሙን "

...በመቃብሩ ዘንድ አዘክሪ

በአለቀሰሽው እንባ "

አሳስቢ ድንግል ሆይ "

ገነት እንድንገባ "

❹❸ አንደበቴም ያውጣ

©ዘማሪት ፋንቱ ወልዴ

አንደበቴም ያውጣ የምስጋና ቅኔ

የአምላኬን ማዳን አይቻለው በአይኔ

በገባአን ሰማይ ጸሃይን ያቆመ

ዛሬም ጎብኝቶኛል እየደጋገመ

...ወጥመድ ተሰበረ እኔም አመለጥኩኝ

ከኃጢያት ፈላጻ ከሞት አተረፈኝ

የአናብስቱን አፍ በሃይሉ የዘጋ

የዳንኤል አምላክ ይኖራል ከእኛ ጋ

...በዳዊት ምስጋና በያሬድ ዝማሬ

ከቅዱሳን ጋራ ልዘምር አብሬ

እርሱን ሳመሰግን ሜልኮል ብትስቅብኝ

ለጌታዬ ክብር እዘምራለሁኝ

...አሰፈሪው ነበልባል እሳቱ ቢነድ

ለጣኦት እንድሰግድ ነገስታት ቢያውጁ

ሁሉም ቢተዉኝ ቢጠላኝም ዓለም

ጽናት ይሆነኛል ጌታ መድኃኔአለም

❹❹ገድሉ ተአምራቱ

©ዘማሪት ፋንቱ ወልዴ

ገድሉ ተአምራቱ እጅግ ብዙ ነው

ጣኦትን አዋርዶ የተሸለመው

የተዋሕዶ ኮከብ ተክለ ሐዋርያ

አባ ተክለ ሃይማኖት ዘኢትዮጵያ

...ዳግማዊ ዮሐንስ ጠፈር የታጠቀው

ንጹህ ባህታዊ ጠላት ያስጨነቀው

የጸጋ ዘአብ ፍሬ ዛፍ ሆኖ በቀለ

በደብረ ሊባኖስ መናኝ አስከተለ

...ደካማ መስሎአቸው በአንድ እግሩ ቢያዩት

ባለ ስድስት ክንፉ ተክልዬ የኔ አባት

እርሱስ አንበሳ ነው ትናገር ደብረ አሰቦ

ሌጊዮን ሲዋረድ እፍረት ተከናንቦ

...ከካህናት መካከል ህሩይ ነው ተክልዬ

መጣው ከገዳምህ ልሳለምህ ብዬ

ኢትዮያጵዊ ቅዱስ አባ ተክለሃይማኖት

ወልድ ዋህድ ብለህ ምድሪቷን ቀደስካት

...የባረከው ውሃ የረገጥከው መሬት

ጥላህ ያረፈበት ሆኗል ጸበል እምነት

ኑና ተመልከቱ ድውያን ሲፈቱ

ይሰብካል ተክልዬ ዛሬም እንደ ጥንቱ

❹❺ስምህ በሁሉ

©ሊ/መ/ ይልማ ሃይሉ

ስምህ በሁሉ ተመስገነ

ከክብር በላይ ክብርህ ገነነ

አንተን ማመስገን ያስደስተናል

ስምህን ማክበር ግብራችን ሆኗል

...አምላክ ተመስገን በሰማያት

ስምህ ይወደስ በፍጥረታት

ከህጻናት አፍ ምስጋና ይውጣ (2)

አንተን ማመስገን ይሁን የእኛ እጣ (2)

...በምግብ እጦት ብንሰቃይም

ማጎሌትህን አናቋርጥም

የመከራ ዶፍ ቢወርድብንም (2)

እንዘምራለን ለአምላካችን ስም (2)

...ሰማዩ ዝናብ ደመናን ቢያጣም

ፍቅርህ በእኛ ውስጥ አላቋረጠም

ቸርነትህን እንጠብቃለን (2)

ካንተ ደጅ ጌታ የት እንሄዳለን (2)

❹❻እመቤቴ የአምላክ እናት

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

እመቤቴ የአምላክ እናት

ላመስግንሽ ቀን ከሌሊት

ለልጅሽም ክብር ውዳሴ

ታቀርባለች ዘወትር ነፍሴ (2)

...ልቤ ተነሳሳ ተቀኘ ለክብርሽ

በፍጹም ትህትና ሊያመሰግንሽ

ጽዮን መጠጊያ ነሽ ለአብርሃም ድንኳን

የታጠረች ተክል እመ ብዙሃን

...የለመለሙች መስክ አምላክ የመረጣት

የጽላቱ ኪዳን ታቦቱ ድንግል ናት

የሰማይ የምድር ንግስት ናትና

ክብር ይገባታል ዘወትር ጠዋት ማታ

...አደራሽን ማርያም የሁሉም እናት

በምልጃሽ አስቢኝ ጐላ ስራቆት

ያንን የእሳት ባህር አሻግሪኝ ድንግል ሆይ

እንዳልወድቅ እንዳልሞት ከቶ እንዳላይ ስቃይ

❹❼የሃይማኖት ፍሬ

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

<u>ተነግሮ የማያልቅ ነው ጸጋህ</u> (2)

በጸሎት የተጋህ የሃይማኖት ፍሬ

ተክለሃይማኖት የእምነቱ ገበሬ

...በወንጌል ብርሃን ህዝቡን እየመራህ

የሃጢአትን ባህር ከፍለህ ያሻገርህ

አተዮጵያዊ ሙሴ በመስቀልህ ባርከን

ፍሬ እንድናፈራ ንጹህ ዘር አድርገን

...ሐዲስ ሐዋርያ አባ ተክለሃይማኖት

ወንጌል ያስተማርከን ለክርስቶስ መንግስት

ጸበልህ እንዲምረን ውረድ አባታችን

በዕጣንህ መአዛ ይፈወስ ደዌያችን

...ለማጠን የበቃህ የሥላሤን መንበር

ሰይጣን ከቶም አይደርስ በሄድክበት ሃገር

ለህሙማን ሁሉ የሆናካቸው ፈውስ

ጠብቀን ተክልዬ በሰጋም በነፍስ

...በጣሙን የበዛ ትሩፋት ምግባርህ

ጸሎትህን ያልተውክ ቢቆረጥ አንድ እግርህ

ምዕራፈ ቅዱሳን የወንጌል ገበሬ

እኛንም አድነን ከዚህ አለም አውሬ

❹❽ናርዶስ ቀጺመታት

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዋድሮስ ዮሴፍ

ናርዶስ ቀጺመታት አሉ በልብሶችሽ መሃል (2)

የገነት ሽቱ ነሽ ሽቱ ነሽ (2) ማርያም ድንግል

...የተከበርሽ ነሽ አንቺ ከፍጥረት

መዓዛሽን ወዷል ጌታ ጸባኦት

ጠላት እንዳይከሰኝ ከጎኔ ሁኚና

ነውሬን ሸፍኚው እናቴ ነሽና

...ገሊላዊት ድንግል የገነት ፈሳሽ

የቀሰለችውን ህይወቴን ፈውሽ

ስዓሊ ለነ ቅድስት በቀን በሌሊት

ለአፌ ጥበብ ነሽ ቅኔ ማኅሌት

...ሁልጊዜ ድህነትን የምንለምንሽ

በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን ያገኘሽ

ክርስቲያኖች ሁሉ ተስፋ የሚያደርጉሽ

ለአለም የሚበቃ ምልጃ ቃልኪዳንሽ

❹❾ የስሙ ትርጓሜ

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዋድሮስ ዮሴፍ

የስሙ ትርጓሜ ማን እንደ እግዚአብሄር ነው

የሰውን ወደ አምላክ የአምላክን ወደ ሰው

እኛን የሚረዳን ዘወትር በምልጃው

የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ነው

...ከጉድጓድ ተጥሎ ፍጹም ከሚያስፈራው

ከተራቡ አናብስት ዳንኤልን ያዳንከው

እኛንም ተራዳን ቸል አትበለን

ሰይጣን በተንኮሉ ወጥመድ ሳይጥለን

...የከፉ ሰው ስራ ክፉ ሃሳብ ነውና

በቅንነት መንገድ ከቶ አይሄድምና

የሞቱን ደብዳቤ ለባሕራን ሲሰጠው

ሚካኤል አጥፍቶ በደስታ ለወጠው

...ገና ብላቴና ሳለው አንድ ፍሬ

ሰው ሁሉ ሲንቀኝ ምስጋናን ጀምሬ

ጸጋዬን አብዝቶ ያበቃኝ ለዚህ ክብር

የሚካኤል አምላክ ይመስገን እግዚአብሔር

❺❶ወላዲተ አምላክ

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

ወላዲተ አምላክ ማርያም ድንግል (2)

ልዩ ነው ክብርሽ (2) ከፍጥረት መሀል

...በቃሉ አለማትን ሳይፈጥራቸው ገና

ታስበሽ የነበርሽ በእግዚአብሔር ህሊና

ከሐና ማህጸን ከኢያቄም አብራክ

እናቱ እንድትሆኚ የመረጠሽ አምላክ

...ከመላእክት በክብር አንቺ ትበልጫለሽ

ከሰዎች ልጆችም የለም የሚመስልሽ

በእግዚአብሔር ዘንድ ስምሽ የገነነ

አልተገኘም ድንግል እንዳንቺ የከበረ

...ነውር የሌለብሽ ንጽህይት ሙሽራ

የመመኪያችን ዘውድ ርህሪተ ህሊና

እናት እና ድንግል ወላዲተ ቃል

የማትለወጪ የሃይማኖት በትር

❺❶ሥላሴን አመስግኑ

©ሊ/መ/ቀ/ ምንዳዬ ብርሀኑ

ሥላሴን አመስግኑ (2)

የምድር ፍጥረታት ዘምሩ እልል በሉ

...በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

ምስጋና ይገባል ከምንም በፊት

አለማትን ሁሉ ለፈጠረ ጌታ

ምስጋና ይገባል ከጧት እስከ ማታ

...ኪሩቤል ሱራፌል የሚያመሰግኑት

መላእክት በሰማይ የሚዘምሩለት

እኛም የአዳም ልጆች እንዘምራለን

በሰማይም በምድር እን ጠራሃለን

...ብራብ በሥላሴ እጠግባለሁኝ

ብጠማም በአምላኬ እረካለሁኝ

ሥላሴ አምባዬ ክብሬ ናቸውና

ሁሌም ይመሩኛል በህይወት ጎዳና

❺❷ሁሉም ነገር ሆነ

©ዲ/ ታዴዎስ ግርማ

ሁሉም ነገር ሆነ በግሸን ማርያም

በደብረ ከርቤ በግሸን ማርያም

በእግዚአብሔር ፈቃድ (2) ሁሉም ነገር ሆነ

...መስቀሌን በመስቀል በግሸን ማርያም

እንዳለው በቃሉ "

በግሸን አደረ "

ግማደ መስቀሉ "

ክርስቲያኖች ሁሉ "

እንዳዝ ከደጇ "

ትኖራለችና "

ድንግል ከነ ልጇ "

...በገነት መስሎ በግሸን ማርያም

ጌታ ያስቀመጠሽ "

አንድ መግቢያ ያለሽ "

ግሸን ደብረ ከርቤ "

የታቦር ተራራ "

ሆነሽ የተመረጥሽ "

ለመስቀል ማደሪያ "

...እንማጸናለን በግሸን ማርያም

ደጇ ሰላም ሆነን "

በእቺ አማላጅነት "

ጌታ እንዲለመነን "

❺❸ መነነ

©ዲ/ ታዴዎስ ግርማ

መነነ ተ/ሃይማኖት መነነ (2)

አሰረ ወንጌል ዴገነ

...በእምነቱ ጸና መነነ

ተጋድሎን ፈጸመ (2) "

ተከልዬ በአንድ እግሩ "

ሰባት ዘመን ቆመ "

...የጽድቅ ሰራን ሰራህ መነነ

የእምነቱ ገበሬ (2) "

ለእኛ አርአያ ሆኗል "

የዘራኸው ፍሬ "

...የኢትዮጵያ ብርሃን መነነ

ተ/ሃይማኖት (2) "

ሀገርክን አሰባት "

ዛሬም አትተዋት "

...በተክልዬ ገዳም መነነ

ዲያቢሎስ ታሰረ "

ለብዙ ዘመናት "

በባርነት ኖረ "

ድንጋይን ፈለጠ "

እንጨትን ሰበረ "

እንዳይነቃነቅ "

በግዝት ታሰረ "

መነነ ገብረ ክርስቶስ መነነ (2)

አሰረ ወንጌል ዴገነ

...እናቱ ለሰርጉ መነነ

ጃኖ አሰርታለት "

አባቱ ለጫጉላው "

ሸር ጉድ ሲልለት "

ከደመቀ ሰርጉ "

ከዚያ ተድላ ደስታ

ጥሎ ተሰደደ ፍቅር ይዞት ከጌታ

...ከደላው ቤት ወጥቶ መነነ

ተጠማ ተራበ (2) "

ከደመቀ ጫጉላው "

ጫካውን ወደደ "

የአባቱን ርስት መነነ

ንግስናውን ትቶ (2) "

ሸፈተ መነነ "

ላይመለስ ከቶ "



ከላይ የቀጠለ

<u>መነነች ከርስቶስ ሰምራ መነነች</u> (2)

አለም በእኔ ዘንድ ሙት ነው እያለች

...ከሞቀ ትዳርዋ መነነች

<u>ጥላ ተሰደደች</u> (2) "

ስለ ጌታ ፍቅር "

ተጠማች ተራበች "

...ለሳጥናኤል ምህረት መነነች

<u>የለመነ ማን ነው</u> (2) "

ያንቺስ ቅድስና "

እናቴ ልዩ ነው "

...አስራ ሁለት አመት መነነች

በባህር የኖረች "

ስለጌታ ፍቅር "

እራሷን የሰዋች "

የሁላችን እናት "

ክርስቶስ ሰምራ ነች "

❺❹ባሕራንኒ

©ዲ/ ታዴዎስ ግርማ

ባሕራንኒ ይቤ (4)

ባሕራንኒ ይቤ አ ዘ ነገደ ባህር

ርኢከዎ ለሚካኤል ወስንኩ ጠይቆቱ ዘይብል (2)

ባህራንኒ ይቤ (4)

...የሞቱን ደብዳቤ ቅዱስ ሚካኤል

ሚካኤል አጥፍቶ ″

ባሕራንን አዳነው ″

በሰርግ ተከቶ ″

ሰዳዴ ሳጥናኤል ″

ሊቀ መላእክት ″

እኛንም አድነን ″

ከሲኦል እሳት ″

...ከሊቀ ነቢያት ቅዱስ ሚካኤል

ከነ ሙሴ ጋራ ″

ህዝበ እስራኤልን ″

ሚካኤል ሲመራ ″

ቀን ደመና ጥሎ ″

ሌሊት እያበራ ″

ተሸገሩ ኤርትራን ″

ሁሉም በየ ተራ ″

❺❺ኦ ክርስቶስ

©ዲ/ ታዴዎስ ግርማ

ኦ ክርስቶስ ኦ አምላክ ብሩህ ነህ

<u>ልቦናዬ አብራው በጥዑም ቃልህ</u> (2)

...የታቦር ደመና ክርስቶስ

የሲና ልምላሜ ″

ምንነው ሙሴን በሆንኩ ″

እንዳይህ ቀድሜ ″

የዮርዳኖስ ውሃ ″

በላይህ ሲፈላ ″

ዮሐንስን በሆንኩ እንዳይህ በተድላ

...ነበልባል ሐመልማል ክርስቶስ

ተዋህዶ ሲና ″

ሙሴ ከሩቅ ሆኖ ″

ተመልክቷልና ″

በቀረበ ጊዜ ″

ነገሩን ሲረዳ ″

ለእስራኤል ሾምኸው ሁሉን እንዳይጎዳ

...ሙሴ በበትሩ ክርስቶስ

ኤርትራን ሲመታ ″

ተሸገሩ እስራኤል ″

በፍጹም ደስታ ″

ያልተደሰቱማ ″

የፈርኦን ሰራዊት ″ እየተሰጠሞ ቀሩ ወደ ውሃሊት



ከላይ የቀጠለ

...ትንቢቱ ጸደቀ የኢሳዪያስ

ድንግልም ወለደች ″

በመንፈስ ቅዱስ ″

ምነው ባደረገኝ ″

እንደ እነ ሰሎሜ ″

ጌታዬ ሲወለድ ለማመስገን ቆሜ

...ሐዋርያቱ ሁሉ ክርስቶስ

ዞረው ያስተማሩት ″

ወንጌልህ ብርሃን ነው ″

የአለም መድኃኒት ″

ዮሐንስ እንዳለው ″

ጥምቀት ለንስሐ ″

እታጠበዋለው የነንህን ውሃ

...ሚካኤል በቀኝህ ክርስቶስ

ገብርኤል በግራ ″

ግሩማን የሆኑ ″

ሁሉም በየተራ ″

ሱራፌል ኪሩቤል ″

ዐይናቸው የበዛ ″

ያመስግኑህል አንተን የአለም ቤዛ

❺❻ነዓ ነዓ

©ዘማሪ ፍቃዱ አማረ

ነዓ ነዓ ሚካኤል ነዓ ነዓ

ነዓ ነዓ ሚካኤል ና ወደኛ

ምህረት ከአምላክህ ለምንልን ለኛ

...የባሕራንን ጽህፈት ሚካኤል ነዓ

የሞቱን ደብዳቤ ″

አንተ ስትለውጠው ″

ተደሰተ ልቤ ″

ሚካኤል መሪ ነው ″

ሊቀ መላእክት ″

እኛንም አድነን ″

ከሲኦል እሳት ″

...ከእሳት ውስጥ ተጥለን ገብርኤል ነዓ

ሃይሉ ከበዛበት ″

ትስፋችን ጽኑ ነው ″

ከላይ ከሰማያት ″

መጣልን ገብርኤል ″

እኛ መህላ ቆሟል ″

የነበልባሉን ሃይል ″

በመስቀል ገስጿል ″



ከታች ይቀጥላል

...ፈታሒ ማጎጸን ሩፋኤል ነዓ

ለጭንቅ ደራሽ "

ድርሳንህ ሚያስገርም "

ለደዌ ፈዋሽ "

እንዳበራህለት "

የጦቢትን ኣይን "

የእኛንም ልቦና "

መጥተህ ኣብራልን "

...ብርሃናዊ መልኣከ ራጉኤል ነዓ

ስልጣንህ ግሩም "

የሀገር ጠባቂ "

መልኣከ ሰላም "

ተስፋዬ ደብዝዞ "

ጨለማ ሲውጠኝ "

በረድኤትህ ከበህ "

ብርሀንን ስጠኝ "

...ስውነቴ ደከሞ ዑራኤል ነዓ

በደዌ ስመታ "

ነፍሴን ሲያንገላታት "

የኃጢኣት በሽታ "

ተአምሩን በማሰብ "

ጸና ተማጽኜ "

ዛሬ እዘምራለው "

በጸበሉ ድኜ "

❺❼ዮም ፍስሐ ኮነ

©ዘማሪ ፍቃዱ አማረ

ዮም ፍስሐ ኮነ (2)

በእንተ ልደታ ለማርያም

...በባርነት ሳለን ፍስሐ ኮነ

ኃጢአት በአለም ነግሳ ″

በድንግል መወለድ ″

ቀረልን አበሳ ″

እግዚአብሔር መረጠሽ ″

ልትሆኚው እናቱ ″

ይኸው ተፈጸመ ″

የዳዊት ትንቢቱ ″

...የሔዋን ተስፋዋ ፍስሐ ኮነ

የአዳም ህይወት ″

የኢያቄም ወሐና ″

ፍሬ በረከት ″

ምክንያተ ድኅነት ″

ኪዳነ ምህረት ″

ድንግል ተወለደች ″

የአምላክ እናት ″

...በሔዋን ምክንያት ፍስሐ ኮነ

ያጣነውን ሰላም ″

ዛሬ አገኘነው ″

በድንግል ማርያም ″

የምስራች እንበል ″

ሃዘናችን ይጥፋ ″

ተወልዳለችና ″

የአለም ሁሉ ተስፋ ″

❺❽ና ና ሚካኤል ናና

©ዘማሪ ወንድወሰን አለሙ

ናና ሚካኤል ናና (2)

አዝናለውና ባንተ ልጽናና

ናና ሚካኤል ናና

...የረዳህ አፎምያን ሚካኤል ናና

ጠላት ሲፈትናት ″

አንተ ነህ ያዳንከው ″

ባህራንን ከሞት ″

ለእነርሱ እንደ መጣህ ″

እኛንም ተራዳን ″

ሚካኤል ደግፈህ ″

ለመንግሰቱ አብቃኝ ″

...ዘመኑ ሲፈጸም ገብርኤል ናና

የአምላክ መምጫው ሲደርስ ″

ገብርኤል አንተ ነህ ″

ያልካት ይበልሽ ደስ ″

ድምጽህን አሰማኝ ″

ነፍሴም ጽድቅን ትልበስ ″

...ቆመህ ጽዋ ይዘህ ዑራኤል ናና

ለእዝራ ሱቱኤል ″

ጥበብ አጠጥተህ ″

እውቀትን ስታድል ″

ተገለጠ ክብርህ ″

መልአኩ ዑራኤል ″

ድኜ በጸበልህ ″

በአውደ ምህረትህ ላይ ″

እኔም ዘመርኩልህ ″

❺❾ አምላክ ባከበራት

©ዲ/ መክብብ ወልደጻዲቅ

አምላክ ባከበራት በተክልዬ ደጅ (2)

በረከት ይገኛል ከጻዲቁ እጅ

...በመካራ ጊዜ ተ/ሃይማኖት በችግሯ ቀን ተ/ሃይማኖት

እንደ ደረስክላት " እግዚኀርያን "

እኛንም ታድን ዘንድ " አንተ ደግ አባት "

መጥተናል ከደጅህ " ከያለንበት "

...ከአምላክ በተሰጠህ ተ/ሃይማኖት በቃልኪዳንህ ተ/ሃይማኖት

ህሙማን የሚያድን " የንፍሮ ውሃህ "

ድውይ የሚፈውስ " ግሩም ጸበልህ "

ዘላለም ይኖራል " በአለም ሲያስጠራህ "

...ለሃያ ዘጠኝ አመት ተ/ሃይማኖት ተከሎ ጦሮቹን ተ/ሃይማኖት

ለእኛ ለልጆቹ " ተስፋ ለቆረጥን "

ደከመኝ አላለም " ቆሞ ሲለምን "

...የቁዱሳን ሃገር ደብረ ሊባኖስ ደብረ ሊባኖስ ደብረ ሊባኖስ

ታጥራ ትኖራለች " በመንፈስ ቅዱስ "

በተክልዬ ጸሎት " ስለተቀደሰች "

ከአድባራት ሁሉ " መክብር ትበልጣለች "

❻❼ደጅ ጠናው

©ሊ/መ/ቀ/ እንግዳወርቅ በቀለ

ደጅ ጠናው ቆይቼ ኪዳነ ምህረትን

ተጽናናሁኝ ረሳው ሀዘኔን

የአምላክ እናት አመቤታችን

ማገስ ሁኚኝ ቀሪው ዘመኔን

...የመከራው ዘመን አለፈ እንደ ዋዛ

አንቺን ተጠግቼ የአለሚን ቤዛ

የልጅሽ ቸርነት የአንቺም ደግነት

ባሪያሽን ሰወረኝ ከአስጨናቂ ሞት

እናቴ ስምሽን ስጠራ አለፈ ያሁሉ መከራ

እንባዬ በፊትሽ ፈሰሰ እምዬ በአንቺ እየታበሰ

ሰላም ለኪ

...ልቤ በአንቺ ጸና ከፍ ከፍም አለ

በጠላቶቼ ላይ አፌ ተናገረ

በማዳንሽ ስራ ባሪያሽ ደስ ብሎኛል

የሃያላሉን ቀስት ልጅሽ ሰብሮልኛል

...እጇ ባዶ ሲሆን ወዳጆቼ ሸሹ

በመርገም ምክራቸው ሊለያዩኝ ሲሹ

እሱ የሰጠኝን እርሱ ወሰደ አልኩቸው

እመቤቴ አለችኝ ብዬ አሳፈርኩቸው

...በአውደ ምህረቱ ሆኜ ስጠራት

ዘንበል ብላ አየችኝ ኪዳነ ምህረት

ሃሳብሽን ምንም የለም የሚመስለው

እረፍት ያገኘሁት እናቴ በአንቺ ነው

❻❶ <u>አባ ሳሙኤል</u>

©ሊ/መ/ቀ/ እንግዳወርቅ በቀለ

አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ

መነኮስ ሃያል እቤቱ ግባ

ታስባርካለህ ሰውን ምድር

ቅርብ ነህ አንተ ለእግዚአብሔር

...የበረሀው መናኝ ግሩም ነው ገድልህ

ምድርን አስባርከሃል ከፍ አርገህ በእጅህ

ተአምር ነው ገዳምህን ላየ

ረድኤት በረከት ገበየ

ልጆችህ በገዳም ውስጥ ያሉ

<u>ሳሙኤል</u> (2) ይላሉ

...አይሻገርብሽ እህልም ታጪአት

ጌታችን ብሏታል ዋልድባን መሬት

እርመት ይዘው ልጆቹ በሙሉ

ቋርፍ ነው ዘውትር የሚበሉ

የላመ የጣመ አለን

ዮርዳኖስ ጸበል ምግብ ሆነልን

...አስኬማውን ለብሶ በገዳም ሲኖር

የትህትና አባት ነው የህግ መምህር

<u>ሀሌሉያን ሄደን አይተን</u> (2)

<u>አብረን ካንተ እንኖራለን</u> (2)

❻❷ <u>የያሬድ ውብ ዜማ</u>

©ሊ/መ/ቀ ምንዳዬ ብርሃኑ

<u>የያሬድ ውብ ዜማ ድንግል እመቤቴ ስጦታዬ ነሽ</u> (2)

<u>በምን አንደበቴ እንዴትስ ባለ ቃል ማርያም ልበልሽ</u> (2)

...ምድርና ሰማዩ ታምርሽን ይንገሩ

ፍጥረታት በሙሉ ስላንቺ ይመስክሩ

ተነግሮ የማያልቅ ድንቅ ነው ስራሽ

ድንግል ሆይ እናቴ አምሳያ የለሽ

ማርያም ድንግል እረዳቴ

የምትደርሺልኝ ነይ ስልሽ በጭንቀቴ

ተአምርሽን በዓይኔ አይቻለው

ጽዮን ሆይ ስልሽ ድንግል ሆይ እጠግባለው

...የእግዚአብሔር ጥበቡ ባንቺ ተገለጠ

የአዳም ዘር በሙሉ ከሞት አመለጠ

የመዳን ምክንያት ማርያም አንቺ ነሽ

ለፍጥረቱ ሁሉ መሰላል የሆንሽ

ምግብ አላውቅ እኔን ሚያስፈራኝ

አንቺ ካለሽኝ በፍጹም አልወድቅም

በፊቲሽም እንድቆም ለምሺጋና

ማርያም ልበልሽ በትህትና

...ትውልዱ በሙሉ ለምሺጋና ይቁም

ባንቺ ስለሆነ የቀረለት መርገም

አዳም ከነ ልጁ በሰማይ በምድር

<u>ማርያም</u> (2) ይበል ተአምርሽን ይናገር

ጨለማውም ከፊቴ ተገፈፈ

ማርያም በምልጃሽ ልቤ አረፈ

ከነኔ ነሽ ስልሽ እጽናናለው

እሳት ገደሉን ሁሉንም አልፈዋለው

❻❸ስምሽን ጠርቼ

©ሊ/መ/ቀ/ምንዳዬ ብርሀኑ

ስምሽን ጠርቼ መቼ አፍራለው

ማርያም ብዬ መች እወድቃለው

የምጽናናበት ስምሽ ነውና

ድንግል ሆይ ላቅርብ ላንቺ ምስጋና

...ጨለማ ውጦኝ በጠላት ሀገር

ለዘመናትም ስረገጥ ስኖር

ዲያቢሎስ ማርኮ ሲያሰቃየኝ

የአለሙን መድሃን ወለድሽልኝ

ከአባቶቼ ርስት ከሀገር ወጥቼ

በአህዛብ ሃገር ስኖር ሸሽቼ

ደርሰሽ አጽናንተሽ አከበርሺኝ

ብቸኝነቴን አስረሳሸኝ

...ድንኳኑ ሞልቶ ሰው ታድሞ

አስተናባሪው በጭንቀት ቆሞ

ምን አቀርባለው ብዬ ስቸገር

ምልጃሽ ደርሶልኝ ዳንኩኝ ከማፈር

ያሰብኩት ሀሳብ ደመና ሆኖ

ቢበተንብኝ እንደ ጉም ተኖ

ይሆናል ያልኩት ሳይሆን ቢቀርም

በእመ አምላክ እኔ ተስፋ አልቆርጥም

...እናት አባቴ ባያስታውሱኝ

ይህች አለም ንቃ ገፍታ ብተወኝ

አንቺ ካለሺኝ ምን እሆናለው

አውሎ ንፋሱን ባህሩን አልፋለው



ከላይ የቀጠለ

ጠላቴ ደርሶ ቢያንገላታኝ

መከራ አብዝቶ ቢያስጨንቀኝ

አላቋርጥም ያንቺነ ምስጋና

ውለታሽ ድንግል አለብኝና

...ክፉዎች ደርሰው ቢዝቱብኝ

አንቺን መውደዴን አያስተዉኝ

በአህዛብ መሀላ ስምሽን ስጠራ

መከታ ሁኚኝ እናቴ አደራ

ጠላቴ ደርሶ ቢያንገላታኝ

መከራ አብዝቶ ቢያስጨንቀኝ

አላቋርጥም ያንቺነ ምስጋና

ውለታሽ ድንግል አለብኝና

❻❹ ጽርሐ አርያም

©ሊ/መ/ቀ ምንዳዬ ብርሀኑ

ጽርሐ አርያም (4)

ክብርሽ ገናና ነው ለዘለአለም

...በመላእክት አለም በሶስቱ ከተማ

በኤረር በኢዮር እንዲሁም በራማ

ውዳሴ ቀረበ ለሰማይ ንግስት

የአምላክን እናት በክብር አየናት

...በበረሀ ያሉ አለምን የናቁ

ውዳሴሽ ደግመው ስምሽን የሰነቁ

አንቺን ስንጠራ ጠላት ገለል ይላል

ማርያም በግርማሽ ከሳሻችን ያፍራል

...ከእግሮ ጀ በታች ጨረቃን ተጫምታ

የክብርን አክሊል በራሶጀ ደፍታ

በቅዱሳን ሁሉ ትመሰገናለች

አለም የዳነባት ድንግል ማርያም ነች

...ብርሃነን ለብሳ በንጽህና አጊጣ

ፍጥረትን ስትባርክ በክብር ተገልጣ

ነፍሳት ተቀደሱ በእምነት ከበዋት

ከበሮን አንስተን እንዘምርላት

❻❺ ተ/ሃይማኖት ፀሃይ

©ሊ/መ/ቀ ምንዳዬ ብርሀኑ

ተ/ሃይማኖት ፀሃይ የአምላክ አገልጋይ (2)

ፀሃይ የአምላክ አገልጋይ (2)

...የኢትዮጵያን ምድር የባረካት (2)

አስተማሪዋ የሆንክላት (2)

ይህንን አውቃ ትዘምራለች (2)

ተ/ሃይማኖት ትጠራሀለች (2)

...አልጫው ጣፍጧል በጸሎትህ (2)

ብርሀን ወጥቷል ለልጆችህ (2)

በቃልኪዳንህ ፍጥረት ጸደቀ (2)

ተአምራትህም በዓለም ታወቀ (2)

...ያከበረህን አምላክ ያከብራል (2)

የናቁህንም እርሱ ይጣላል (2)

ፍርፋሪህን ልቤ ናፈቀች (2)

ያንተን በረከት ስለወደደች (2)

...በእግዚኀረያ በጸጋ ዘአብ ተማጽኛለው

ነፍሴን በእጅህ ሰጥቼሀለው (2)

ካንተ ጋር ልኑር ለዘላለም (2)

የሚለያየን ማንም የለም (2)

❻❻ ክንድህን እጠፍ

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ የሴፍ

ክንድህን እጠፍ የሚልህ ማን ነው

ማዳንህን ተው የሚልህ ማን ነው

ቢከፋቸውም አሳዳጆቼ

እሳካሁን አለው በአንተ ጸንቼ (2)

...ማለፌ ሲቀር ህየወት ሲመላ

ሲያልፍ ከላዬ የሞቴ ጥላ

ለምን አዘኑ ሰዶቃውያኑ

ስለከፈሰቸው ላይቀር ማዳኑ

...በባህሩ ዳር ህመሜን ትቼ

አልጋዬን ባዝል ድኜ በርትቼ

በሰንበት ዳነ ማረው ብላችሁ

ያዳነህ ይሙት ለምን አላችሁ

...ስምዖን ዞር በል ይከፈት በሩ

ይብቃኝ ሲምረኝ ማንጎራጎሩ

ኃጢአቴን ፈቅዶ ጌታ ከተወው

ምንህ ተጎዳ በእንባዬ ባጥበው

...በግንባሬ ላይ ዓይኔን ቢሰራ

ቢደባልቀኝ ከሚያዩት ጋራ

ፊታቸው በሀዘን ለምን ጠቆረ

ሁሉኑ ቻይ ጌታ ስለከበረ

...አትዝጉት ደጁን እንመላለስ

የተወደደው በእኛ ላይ ይንገስ

የምናቀርበው ለጌትነቱ

የከበረውን ይዘናል ሸቱ

❻❼ይበራል በክንፉ

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

ይበራል በክንፉ ምልጃውም ፈጣን ነው

የአምላክ ስም አለበት ስሙ ሚካኤል ነው

ያሳደገኝ መልአክ ዛሬም ከእኔ ጋር ነው (2)

...ከፊት የቀደመ ደመናን ዘርግቶ

እንዳልደናቀፍ ጉድባዎቼን ሞልቶ

ዛሬ ላለሁበት ብርቱ ጉልበት ሆነኝ

ሰው ለመባል በቃው ሚካኤል ደገፈኝ

...በእናቴ እቅፍ ገብቼ መቅደሱ

አለው እሰከ ዛሬ አጥሮኝ በመንፈሱ

የህይወቴን ሰልፎች አልፍኩ ከእርሱ ጋራ

ተጽፏል በልቤ የሚካኤል ስራ

...በዙሪያዬ ተክሎ የእሳት ምሰሶውን

ጽድቅ እየመገበ አሳደገኝ ልጁን

የአምላኬን ምስጋና ዘውትር እያሰማኝ

እርሱ ነው ሚካኤል በመዝሙር የሞላኝ

...ፊት ለፊት ተተክሎ ከታናሿ መንደር

ይሰማኝ ነበረ ቅኔው ሲደረደር

ይወሰደኛል ደጁ አየቀሰቀሰ

ታላቁን በረከት በውስጤ አፈሰሰ

...ሴኪሜን እንዳላይ ክንፎቹን ጋረደ

መራኝ ወደ ህይወት መዳኔን ወደደ

የሞአብን ቋንቋ ከአፌ ላይ አጥፍቶ

በጸጋው ቃል ቃነኝ በበረከት ሞል

❻❽የፍቅር እናት

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

የፍቅር እናት የሰላም (2)

ይናፍቀኛል ስምሽን ሳልጠራው ስቀር ማርያም

...በህይወቴ ውስጥ በኑሮዬ

ቅደሚ ከፊት ከውህላዬ

ተደላደለ ልቤ

አንቺ አለሽ ና ከአጠገቤ

ምኞቴም ይስመር ድብቅ ህልሜ

ልለፍ ወጀቡን ተቋቁሜ

የጌታዬ እናት ነሽ

ሃይልን ያደርጋል ጸሎትሽ

...እንዴት እቀራለው ከመንገዴ

አደራ እናቴ አስቢኝ

ለሚያስጨንቀኝ ጠላት

ለሚያሳድደኝ አትስጪኝ

...ትላንትም ዛሬም አመስጋኝ ነኝ

የለም ለነገ የሚያስፈራኝ

ሜዳው ይሆናል ተራራ

ልጅሽ እስካለ ከእኛ ጋራ

❻❾ባለውለታዬ

© ሊ/መ/ዲ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

ባለ ውለታዬ (2)

ከአመድ ያነሳኸኝ ከትቢያ ተጥዬ

ተመስገን ጌታዬ

...በሩን ቢዘጋብኝ ስምዖን ጨከኖ

ዝቅ አድርጎ ቢያየኝ ከአይሁድ ጋር ሆኖ

እንድቀርብ ወደ እርሱ አዘዘኝ ጌታዬ

እግሩን አጥበዋለው ወድቄ በእንባዬ (2)

...የቀራጭ ሃለቃ ቢሆንም ስራዬ

እንድቀርበ ወደ እርሱ አዘዘኝ ጌታዬ

ማእረጌን መሸከም እስኪያቅተኝ ድረስ

ቤቴ ተባረከ በኢየሱስ ክርስቶስ (2)

...ድንጋይ የጨበጡ ቀራጮች ከበውኝ

ነውሬን ዘርዝረው ጌታ ፊት አቆሙኝ

ፈረደችባቸው ኃጢአትም በእነርሱ

በሰላም ሂድ ብሎ ምሮኛል ንጉሱ (2)

...የማምነውን አምላክ አውቀዋለው እኔ

በሰራልኝ ስራ በእድሜ በዘመኔ

ፍቅሩን ተሸክሟል የልቤ ትከሻ

ልለየው አልችልም እስከ መጨረሻ (2)

❼❿ ማርያም ማርያም ብዬ

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

ማርያም ማርያም ብዬ ስምሽን ልጥራው

አይደክመኝም እኔ ብደጋግመው

አሁንም ጠራሁሽ አላስችልህ ቢለኝ

አውቀዋለው ስምሽን እናቴ ስትወልደኝ (2)

...ገና በማህጸን በእናቴ ምጥ ቀን

ደጋግሜ ሰማው ሲጠሩ ስምሽን

በሰከንዳት እድሜ የማውቃት አንዲት ቃል

ልቤ ላይ ያለው ስም ማርያም ማርያም ይላል (2)

...ሔዋን ምጢ ቀሎ ልጆቿን ታቀፈች

በአማላጅነትሽ እናቴም ታመነች

በተወለድኩበት በመጀመሪያው ቀን

ስምሽን እየሰማው ወጣው ከማኅጸን (2)

...ከቃል ኪዳን ስም ጋር አደኩኝ አብሬ

ምልጃሽ ሳይለየኝ አለው እሰከ ዛ ሬ

የህይወቴን ፊደል ባንቺ ላይ ቆጠርኩኝ

በልጅሽ አምኜ ዳግም ተወለድኩኝ (2)

...የከፉ ቀን ስንቄ ያዘልኩሽ በልቤ

የህይወቴ ምግብ የእንጀራ መሶቤ

እንደ ትላንትናው ዛሬም ጠራሻለው

የመስቀል ስር ክብሬን እንዴት እረሳለው (2)

❼❶ወደ ቀድሞ ነገር

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

ወደ ቀድሞ ነገር እንመለስ

የአምላክን እናት እናወድስ

ከፍቅሯ ርቃችሁ የምትኖሩ (2)

ማርያም ፊደል ናት ኑ ተማሩ (2)

...ቃል ተጽፎባታል የመዳኛ ፊደል

ጥበብ የሚሞላ ጨለማን የሚሰቅል

ለቃል ሲጋ መሆን ምክንያት ስለሆነች

ቀርባችሁ ተማሩ ማርያም ፊደል ነች

...አዲሱ ቃልኪዳን ከላይ የተጻፈው

በገሊላ ናዝሬት ገብርኤል ያበሰረው

በማርያም እቅፍ ላይ ታገኙታላቹ

የሚስጢር መዝገቡን አንብቡ ገልጣቹ

...ያዘለችው ወንጌል ቃሉ ያፈውሳል

አምኖ ላነበበው ነፍስ ያለመልማል

በጀርባዋ ያለው እግዚአብሔር ነውና

አቅርቡ ለማርያም ውዳሴ ምስጋና

...ቡዙዎች ተማሩ ስሟን እየጠሩ

በአባታቸው መንግስት እንደ ጸሀይ በሩ

ከብረ ልዕልናዋን ገብርኤል ነግሮናል

ካወደሷት ጋራ ለከብሯ ቆመናል

❼❷እናት አለኝ

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

እናት አለኝ የምታብስ እንባ

አያታለው ስወጣ ስገባ

ኪዳነ ምህረት (3)

አንባ መጠጊያ ናት

...ሔዋን ሰጥታኝ ከበለሱ ፍሬ

እራቆቴን ብቆምም አፍሬ

ልብሴን ይዘሽ ወደ እኔ ቀርበሻል

ደጓ እናቴ ቤቴን አድምቀሻል

ኪዳነ ምህረት (3)

አንባ መጠጊያ ናት

...ከጥፋቱ ውሀ ማረፊያዬ

መርከቤ ነሽ ከሞት ማምለጫዬ

የአምላክ እናት ምልጃሽ ሆኖኝ ክብሬ

በህይወት አለው ጥልቁን ተሸግሬ

...በእናትነት ህይወቴን ጎብኝታ

ልቤ አረፈ ተነቅሎ በሽታ

ሰንሰለቴ ከእጄ ተቆረጠ

መራራዬ በልጅሽ ጣፈጠ

...ለዘላለም ንጽህይት በመሆኗ

ከኔ ጋር ነው ህያው ቃልኪዳኗ

ድስተኛ ነኝ ሀዘኔን አልፌ

አጽናኝ ሆናኝ የመስቀል ስር ትርፌ

❼❸እረድተሀል እና

©ሊ/መ/ቀ/ ምንዳዬ ብርሃኑ

እረድተሀል እና ባሕራንን

ሚካኤል ጠብቀሀል እና ቲዮብስትያንን

ሚካኤል አማልደን አስታርቀን ሚካኤል

...ከሰማያት ስትወርድ ሚካኤል

ለሰው ልጆች ስትራራ ″

ከክብርህ የተነሳ ″

መላው ምድር ነበራ ″

በመከራዬ ጊዜ ″

ፈጥነህ የደረስክልኝ ″

ከአምላኬ ተልከህ ″

ከጭንቅ የገላገልከኝ ″

...አልተረዳሁትም ሚካኤል

በእጇ ያለውን ″

የሞቴን ደብዳቤ ″

የሸሸኩትን ″

ልጨብጥ ስጣደፍ ″

የሰይፉን ስለት ″

የመላእክት ሀለቃ ″

አዳነኝ ከሞት ″

...ገና ህጻን ሳለሁኝ ሚካኤል

አሳድገኸኛል ″

ከብዙ ፈተና ″

አንተ አድነኸኛል ″

አሁንም ጠብቀኝ ″

ቸል አትበለኝ ″

አባቴ ሚካኤል ″

ልጇሆይ በለኝ ″

❼❹ደጉ መልአክ

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

ሃያል ነህ አንተ ሃያል (2)

ደጉ መልአክ ገብርኤል (2)

ይውደቅ ይሸነፍ ጠላት

አንተ ተራዳን በእውነት

...በዱራ ሜዳ ላይ ገብርኤል

ጠኡት ተዘጋጅቶ ″

ሊያመልኩት ወደዱ ″

አዲስ አዋጅ ወጥቶ ″

ሲድራቅ እና ሚሳቅ አብድናቆም ጸኑ

ጣኡቱን ረግጠው በእግዚአብሔር አመኑ

...ተቆጣ ንጉሱ ገብርኤል

በሶስቱ ህጻናት ″

ጨምሯቸው አለ ″

ወደ እቶን እሳት ″

ከሰማይ ተልኮ ወረደ መልአኩ

ከሞት አዳናቸው በእሳት ሳይነኩ

...ከእቶኑ ስር ሆነው ገብርኤል

ዝማሬ ተሞሉ ″

ገፍተው የጣሏቸው ″

በእሳቱ ሲበሉ ″

አልተቃጠለችም የራሳቸው ጸጉር

አዩ መኳንንቱ የእግዚአብሔርን ክብር



ከላይ የቀጠለ

...ናቡከደነፆር ገብርኤል

እጁን ባፉ ጫነ ”

ሰለስቱ ደቂቅን ”

ከእሳት ሰላዳነ ”

ይከበር ጌታ አለ የላከው መልአኩን

ሊያመልከው ወደደ ሰላየ ማዳኑነን

❼❺ አለ ለኔ

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

አለ ለኔ የተሻለ ነገር (2)

ዛሬን ባዝን ለጊዜው ብቸገር

አለ ለኔ የተሻለ ነገር

...በእጇ የጨበጥኩት በድንገት ቢበተን

ዙሪያዬን ቢከበኝ ያላሰብኩት ሀዘን

እንባዬ በደስታ መቀየሩ አይቀርም

እተማመናለው በጌታዬ አላፍርም

...ሀብቴን ልጇን ባጣ እርሱ እንደ ወደደ

የኢዮብ መከራ በእኔ ከወረደ

እራቆቴን መጣው እንዲሁ እሄዳለው

ከዚህ የላቀውን ከእርሱ እጠብቃለው

...መከራው ቢከብደኝ ከዙፋን ወርጄ

ከርስቴ ብሰደድ በአቢሴሎም ልጄ

ቀኑ እሰከሚነጋ አልፈራም ጨለማ

ዳግም እለብሳለው የጽዮንን ግርማ

...አሳዳጇ ቢያይል ጉልበቱ ቢጸና

ተግዳሮቱ በዝቶ ወደ እኔ ቢያቀና

የከበረው ድንጋይ አለ በወንጭፉ

እቋቋመዋለው እርሱን ተደግፌ

...በናባው ተራራ ቢሆን መቃብሬ

ከነአን ባልገባ ከእርሱ ጋር አብሬ

አለኝ በሰማይ ቤት እጅግ የከበረች

በጆሮ ያልተሰማ በአይንም ያልታየች

❼❻ በማህጸን ቅኔ

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

በማህጸን ቅኔ በማርያም ተሰማ

በተራራማ ሀገር በኤፍሬም ከተማ

ዮሐንስ ይናገር በረሀ ያደገው

ድንግል ስትናገር ምን እንዳዘለለው

...የእናቱ ማህጸን የቅኔ ርስት ሆነች

ድንግል የአምላክ እናት ፊቱ ስለቆመች

በሀዜት ዘመረ ዘለለ በደስታ

ከድንግል ሲወጣ ታላቁ ሰላምታ

...በድንግል ማህጸን ስላየ ጌታውን

ከመወለድ ቀድሞ ሰማነው መዝሙሩን

ትንቢቱ ሲፈጸም በሆዷ ሲደርስ

ሰገደ ለአምላኩ የስድስት ወር ጽንስ

...ጀመረ ስብከቱን ገና ሳይወለድ

ተፈጥሮ መች አለ ነቢዩን ለማገድ

አፉ ተከፈተ በታላቅ ምስጋና

በእናቱ ማህጸን ድምጽን አሰማና

...የዮሐንስ እናት ኤልሳቤጥ ገረማት

ልጇ በማህጸን ቅኔ ሲቀንብት

ድምጿን ከፍ አረገች ዓለም እንዲማ

ሞላት መንፈስ ቅዱስ በመዝሙር በዜማ

❼❼ሞገድ ሲመታኝ

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

ሞገድ ሲመታኝ ማዕበሉ

ማን ያድነዋል ሁሉም ሲሉ

በሰላም አለፍኩ በጸጥታ (2)

ሁሉ ተችሎ ላንተ ጌታ (2)

...በአንተስ ቁስል ተፈወስኩኝ

ጌታ በፍቅርህ ተማረኩኝ

ሞቴን ሽረኸው በአንተ ሞት (2)

ይኸው አቆምከኝ በህይወት (2)

...ደጅ ስጠናህ ስማጸንህ

መቼ ጨከነ ጌታ ልብህ

እንደ ቀራጩ አጎነበስኩ (2)

ምህረት ጸጋህን ከእጅ ለበስኩ (2)

...ዘውትር እልል ብል ብዘምር

ስለገባኝ ነው ያንተ ፍቅር

ጌታ ብጠራው ስምህን (2)

ለውጠኸው ነው ታሪኬን (2)

...ዓይኖቼ ኢያዩም ካንተ በቀር

የምትወደድ ምትፈቀር

ዘመድ ወገኔ ሆነኸኛል (2)

እኔን የሚችል የት ይገኛል (2)

❼❽ተ/ሃይማኖት ባህታዊ

©ዘማሪት ጸዳለ ጎበዜ

ተ/ሃይማኖት ባህታዊ

ምድራዊ ሲሉህ ሰማያዊ

መአደባባዩ ተተክለሀል

ተክልዬ መልካሙን ፍሬ አፍርተሀል

...ቃል ኪዳን አለህ የገነነ

ምህረት የሚያሰጥ የታመነ

በስምህ ውሀ አጠጥተን

ዋጋችን በዝቷል አባታችን

...እኛም ሆነናል ልጆችህ

ማርኮ አስቀርቶ ምግባርህ

በምልጃህ ፀሎት ትሩፋት

ቤታችን ሞላ በረከት

...ምህረት ይዘንባል ከሰማይ

በአንድእግርህ ቆመህ ስትፀልይ

ብዙ ተጋድለህ አትርፈሃል

ያገለገልከው አእክብሮህል

...ተሰባበሩ ጣኦታቱ

አምነው ሰገዱ መካንንቱ

የበረታው ቃል ከአፍህ ወጥቶ

የአምላክ አድርጓል ሁሉን ገዝቶ

❼❾ገብርኤል ስለው ሰምቶ

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

ገብርኤል (2) ስለው ሰምቶ

መጣ ወደኔ ፈጥኖ

ሰንሰለቴን በጠሰው

የአንበሶቹን አፍ ዘግቶ

...ገብርኤል ስጋዬ ሳይረግፍ በአናብስቱ ጥፍር

" ታድጎኛል ምልጃው የመልአኩ ክብር

" በራብ ለነደዱ አናብስት ሲጥሉኝ

" አንተ አለኽኝና ከንፎችህ ከለሉኝ

...ገብርኤል ከአፎቱ ሲመዘዝ የጠላቴ ሰይፍ

" አጽንቶ ይዞኛል ፍሬዬ ሳይረግፍ

" አደገድጋለው አለኝ እና ፍቅሩ

" በእሳት ከንፉ ታጥሯል የደጇ ድንበሩ

...ገብርኤል በሰይፍ ተመትሯል የክፉዎች ክህደት

" ሀብሉ ተበጣጥሷል የአመጹ ሰንሰለት

" ከቅዱሱ ድንጋይ ህይወት ከሚያፈልቀው

" እንዳልለየ ረዳኝ ክብሬን ከፍ አረገው

...ገብርኤል አለው ልዩ ስልጣን ከአምላክ የተሰጠው

" ይመጣል ወደ እኛ እሳቱን ሊያጠፋው

" እኛም እናምናለን ሰምተናል አይተናል

" የመላእክት ሀለቃ ከአምላክ ያማልዳል

❽❼ገና እንዘምራለን

©ሊ/መ/ ይልማ ሃይሉ

ገና እንዘምራለን (4)

እንደ መላእክቱ ብርሃንን ለብሰን

ገና እንዘምራለን

...ወላዲተ አመላክን ከፊት አስቀድመን

በዳዊት በገና መሰንቆ ታጅበን

ለሥላሴ ክብር ገና እንዘምራለን

ገና እንዘምራለን

...በምስጋና ስርአት ከሰለጠኑት ጋር

ልብን የሚያስደስት መዝሙር እየዘመርን

ያልተሰማ ዜማ ያልታየ ምስጋና

ይፈልቃል አይቀርም ከእኛ ልቦና

ገና እንዘምራለን

...በትዕቢት ሳይሆን በታላቅ ትህትና

በልዩ ተመስጦ በፍቅር ልቦና

ስራችን ይሆናል የአምላክ ምስጋና

ገና እንዘምራለን

...ዳዊት በተመስጦ እርቃኑን ቢሆንም

ሜልኮል በዝማሬው ብትሰቅበትም

አምላክ ከወደደ እንዲያመሰግነው

በደስታ እንዳይዘምር ከልካዩ ሰው ማን ነው

ገና እንዘምራለን

❽❶ አረሳት ኢትዮጵያን

©ሊ/መ/ ይልማ ሃይሉ

አረሳት ኢትዮጵያን በእርፈ መስቀል

አባ ተ/ሃይማኖት ሰባኬ ወንጌል

የእግዚአብሔር ሰው ነው ተወዳጅ በሰማይ

የተረማመደው በጽድቅ አደባባይ

...ፈውስ እና ጸሎቱ ቃሉ የተሰማ

ወንጌል የሰበከ በገጠር ከተማ

የኢቲሳው ኮከብ የደብረ አስቦቱ

ለወንጌል ተዋጋች ብጽእይት ህይወቱ

...ፋናው እስከ ዛሬ ሲያበራ የኖረው

የኢቲሳው አባት ፍስሐ ጽዮን ነው

እግዚእሃረያ እናቱ ማህጸነ ቡሩክ

ወለደች ኮከብ ሲኦልን የሚያውክ

...ዲያቢሎስ እስከ አሁን ስሙ ሲጠራበት

ሲረገጥ ይኖራል በእሳት ሰንሰለት

ሐዲስ ሐዋርያ የኢትዮጵያ አባት

ደጋና ቆላውን በመስቀል ባረካት

...ምንጩና ፏፏቴው ተራራው ቅዱስ ነው

የአባታችን መስቀል ጸሎት ስለነካው

የተራመደበት የዳሰሰው ሁሉ

ድውይ ይፈውሳል ሳርና ቅጠሉ

❽❷ያዕቆብ ከቤርሳቤ

©ሊ/መ/ ይልማ ሃይሉ

ያዕቆብ ከቤርሳቤ ወደ ካራን ሲሄድ

የለውም ነበረ አማካሪ ዘመድ

ጸሀይ ጠልቃ ነበረ ከዚያ እንደ ደረሰ

ከእራሱ በታች ድንጋይ ተንተራሰ

...ህልምንም አለመ ታላቁን ራዕይ

መሰላል ተተክሎ ከምድር እስከ ሰማይ

ሲወጡ ሲወርዱ ማላእክት በእርሷ ላይ

እግዚአብሔርም ቆሞ ከላይ ከጫፏ ላይ

...የአባቶችህ አምላክ እኔ እግዚአብሔር ነኝ

ይህንን ለርስትህ እሰጥሀለሁኝ

ዘርህ እንደ አሸዋ በምድር ይዘራል

በአራቱም ማዕዘን ህዝብህም ይሆናል

...አበው በምሳሌ እንደ ተናገሩት

ከምድር እስከ ሰማይ አምላክ የዘረጋት

በላያ ተቀምጦ በግልጽ የታየባት

የያዕቆብ መሰላል እመቤታችን ናት

...ሰማይ እና ምድር የሚታረቁባት

ወልደ እጓለ እመ ህያው የተገለጠባት

መላእክት በሰማይ በአንድ የዘመሩላት

ታላቋ መሰላል እመቤታችን ናት

❽❸ገብረ ሕይወት

©ሊ/መ/ቀ/ እንግዳወርቅ በቀለ

ገብረ ሕይወት (4) ከንሂሳ መጣ ሊባርካት

ኢትዮጵያ መጣ ሊጠለልባት

...ገብረ ሕይወት በዝቋላ ገዳም

" መቶ አመት ጸለየ

" አባታችን ለኛ

" ጌታን ተማጸነ

" በባህር ውስጥ ጠልቀህ

" ማርልኝ ብለሀል

" ለኢትዮጵያውያን

" ምህረት ለምነሀል

...ገብረ ሕይወት አንበሳና ነብር

" ይከታተሉሀል

" በጸጋህ ተማርከው

" ላንተ ተገዝተዋል

" የቅዱሳን ራስ

" ገብረ መንፈስ ቅዱስ

" ቃልኪዳን ተሰጠህ

" ምድረ ከብድ ስትደርስ

...ገብረ ሕይወት የእናትህን ጡት ሳትቀምስ

" የኖርክ በበረሀ

" ልብስህ ጸጉር ብቻ

" እጹብ የአምላክ ስራ

" እንማጸናለን

" ሁላችን መአንድነት

" ጸሎተህ እንዲያወጣን

" ከኃጢአት ከመቅሰፍት

❽❹ በአለት ላይ ነውና

©ሊ/መ/ቀ/ ምንዳዬ ብርሀኑ

በአለት ላይ ነውና ያቆማት አጽንቶ

በደሙ ነውና የቀደሳት ዋጅቶ

ይጠብቃልና ጠባቂዋ ተግቶ

<u>የገሀነም ደጆች አይችሏትም ከቶ</u> (2)

...መንጋዋን ሊበትን ተኩላ ቢበረታ

ማዕበሉ መርከቧን ፍጹም ቢያንገላታ

የተቃወሟትን ሁሉን ድል ነስታለች

ዛሬም እንደ ጸሀይ ይኸው ታበራለች

...የቄርሎስ እናት ናት የዲዮስቆሮስ

የአሮኔዎስ እና የነ ፊሊጶስ

የወለተ ጴጥሮስ የክርስቶስ ሰምራ

የጴጥሮስ እናት ናት የነ መስቀል ክብራ

...ኑፋቄ ቢነሳ ክህደቱ ቢነፍስ

ዙሪያዋን ቢከቧት ቅጥሯን ለማፍረስ

የጸና ነውና በደም ተመስርቶ

ትረታለች እንጂ አትረታም ከቶ

...አእላፍ መላእክት ዙሪያ ከበዋታል

አእላፍ ቅዱሳን የጸልዩላታል

እኛ ማናቃቸው እርሱ የሚያውቃቸው

ለእርሷ የሚሰሩ እጅግ ብዙ ናቸው

❽❺ አባ አባ

©ሊ/መ/ቀ/ እንግዳወርቅ በቀለ

አባ አባ ተ/ሃይማኖት አቡየ (2)

በለኒ በለኒ ወልድየ

...አባ አባ እንኳን ሰው ምድሪቱን

" ጾም አያሳድርም

" አምላከ ተክልዬ

" ብዬ አፍሬ አላውቅም

" ምድራዊ መልአከ ነህ

" የኢቲሳ አንበሳ

" ለደብረ ሊባኖስ

" አንተ ነህ ሞገሷ

...አባ አባ ስምዐኒ ብያለው

" ሳለህ በሰማይ

" ከኪሩቤል ተርታ

" ሆነህ ስትታይ

" ስምህም ሲጠራ

" ገድልህ ሲነገር

" እጹብ ድንቅ ያሰኛል

" የተሰጠህ ክብር

...አባ አባ አባቴ እልሀለው

" ልጄ ሆይ በለኝ

" የአባትና የልጅ

" ፍቅርህ ይጽናልኝ



ከላይ የቀጠለ

" ንፍሮ ውሃ ጠጥቼ

" ተአምር አይቻለው

" እባብና ጊንጡን

" ተረማምጃለው

...አባ አባ እለት በእለት ሄጄ

" ደጅ ስጠናው

" ይሰማል ተክልዬ

" ዛሬም ህያው ነው

" እንቆቅልሽ ፈቶ

" ደስ አሰኝቶኛል

" የተ/ሃይማኖት

" ቡራኬ ደርሶኛል

❽❻ስድቤን አርቀሽ

©ሊ/መ/ቀ/ እንግዳወርቅ በቀለ

ስድቤን አርቀሽ ነውሬን ሸፈንሽው

እመ አምላክ ባንቺ መቼም አላፍርም

ስምሽን ጠርቼ እጽናናለሁኝ

ሃዘኔን ባንቺ እረሳለሁኝ

...ነውር አለብኝ ብዙ ስድብ

አንጀት የሚልጥ ልብ የሚያቆስል

ስሜን ለውጠው ሲያንቋሸሹኝ

በሀዘን በለቅሶ ድንግል መጣሁኝ

እንደ ሐና ሆኜ በቤተ መቅደስ

በመረረ ሀዘን ነው እኔ ማለቅስ

ፍረጂልኝ እና ልመለስ ከቤቴ

ሃዘኔን በደስታ ለውጪው እናቴ

በግራ በቀኝም ጠላት ቢከበኝ

አብዝቼ እጮሀለው እናቴ ስሚኝ

...መከራው በዝቶ ግራ ገብቶኛል

ድምጽሽን ልስማው ያረጋጋኛል

የሰው ህይወቱ ብርቱ ሰልፍ ነው

ደስታ እና ሃዘን የማይለየው

በእጃችን ወድቋል ሲሉኝ ጠላቶቼ

አመለጥኳቸው ስምሽን ጠርቼ

ሰው የዘራውን ያንኑ ያጭዳል

በቆፈረው ጉድጓድ እራሱ ይገባል

እናቴ እመቤቴ ብዬ ስጠራሽ

ከመከራ ሁሉ ታቀጪኛለሽ



ከላይ የቀጠለ

...በምርኮ ሳለው በሰው ሀገር

ግፍ ጥለውብኝ ስኖር በእስር

ምልጃሽ ደርሶልኝ ተፈውሻለው

በተአምራትሽ እኔ ድኛለው

ቃልሽን ሰምቶ ጽንሱ ዘለለ

ብላለች ኤልሳቤጥ ነውሬ ተወገደ

የጌታዬ እናት እኔን አሰበችኝ

ታሪኬን ቀይራ ይኸው ባረከችኝ

የእመቤቴ ከሆነኩ ማን ይቃወመኛል

ወጀቡም ማዕበሉም ይታዘዙልኛል

...ወይኑ እኮ አልቋል የዶኪማስ ቤት

ድንግል አማልጂው ነይ የእኛ እመቤት

ስምሽ ሲጠራ በየቦታው

ይሞላልና የጎደለው

ግራ የገባው የቸገረው

ድንግል ይጥራ እንድትረዳው

ሳዝን ስተከዝ የምታጽናና

እናት አለቺኝ ርህሪተ ህሊና

እናቴ እመቤቴ ብዬ ስጠራሽ

ከመከራ ሁሉ ታወጪኛለሽ

❽❼ቢያበሉኝ ቢያጠጡኝ

©ሊ/መ/ቀ/ ምንዳዬ ብርሃኑ

ቢያበሉኝ ቢያጠጡኝ ፈትፍተው ቢያጎርሱኝ

ያሻኸውን ውሰድ ሁሉ ያንተ ነው ቢሉኝ

እኔስ እነደ ስሟ የጣፈጠ አጣሁኝ (2)

...የዚህ ዓለም ነገር ባዶሆኖብኛል

ዛሬ የበላሁት ነገ ይርበኛል

መራራው ህይወቴ ጣፋጭ የሚሆነው

እመቤቴ ስሚኝ ባንቺ ጨውነት ነው (2)

...አንቺ የሌለሽበት ማእዴ ባዶ ነው

ስምሽን ካልጠራው ጣፋጭ መራራ ነው

በእጇ ከጨበጥኩት የመሶብ እንጀራ

ማርያም የሚለው ስም ጣፋጭ ነው ሲበላ (2)

...ተስፋ ያደረገ አንቺን በህይወቱ

ስለሆንሽለት ነው ለተማሪ እራቱ

እኔም እልሻለው የኑሮ ጣእሜ

ከሞት ወደ ህይወት መሸጋገሪያዬ (2)

88 የልቤን ሁሉ

©ዘማሪት ፋንቱ ወልዴ

የልቤን ሁሉ ለማን ለማከር

እመቤቴ ሆይ ካንቺ በቀር

ለደካማ ሰው መጠጊያ እኮ ነሽ

ሀዘን ጭንቀቴን የምረሳብሽ

...ቅዱሳን አበው አንቺን መረጡ (2)

ከሲኦል አለም ስላመለጡ

ጻዲቅ በስራው ያኔ ሲድን (2)

እጠራሻለው ድንግል አንቺን

...የጭንቄ ደራሽ አከሊሌ ነሽ (2)

ቂም በቀል አያውቅ የዋህ ልብሽ

ልቤ ለፍቅርሽ ሰፊ ስፍራ አለው (2)

በአዘንኩኝ ሰአት እጠራሻለው

...ዋሴ ነሽ ለኔ ድንግል እናቴ (2)

ስምሽ ጠበቀኝ ከልጅነቴ

ሁል ጊዜ ለኔ በጎ አረግሽልኝ (2)

ምን ልበል ላንቺ ቃላታም የለኝ

...ላዘንኩኝ ለኔ ደስታዬ ነሽ (2)

ያረጋጋሽኝ ፈጥነሽ ደርሰሽ

ስምሽ ታጥአንን የሚቀድስ (2)

ከሞት ወደ ህይወት የሚመልስ

...የመንገዴ ስንቅ የረሀቤ መርሻ (2)

ለታመመ ሰው ነሽ መፈወሻ

ለተማጸነሽ በስምሽ አምኖ (2)

ማን አፍሮ ያውቃል አንቺን ለምኖ

89 በጎ መአዛ

©ዘማሪት ፋንቱ ወልዴ

በጎ መአዛ ሽታዬ ነሽ

በሰው ሁሉ ፊት ዘመርኩልሽ

<u>ባንቺ ጣፈጠ አልጫነቴ</u> (2)

<u>እጠራሻለው ነይ እመቤቴ</u> (2)

...ምሳሌ የሌለሽ ነዪ እመቤቴ ዘመዴ ነሽ ነዪ እመቤቴ

ያን ከፉ ዘመን " ያለፍኩብሽ "

በፍቅርሽ እሳት " ልቤ ነደደ "

እናትነትሽን " ስለወደደ "

...የሰውስ ጉልበት ነዪ እመቤቴ ምን ይረባኛል ነዪ እመቤቴ

ሰረገላዬ " መች ያድነኛል "

ከተሰወረው " ክፉ መከራ "

አድናለሁኝ " አንቺን ስጠራ "

...ለስንፍናዬ ነዪ እመቤቴ መቼ ልክ አለው ነዪ እመቤቴ

ስለ በደሌ " እተክዛለው "

ላነጋገሬ " ማጣፈጫ ነሽ "

ተሰምቻለው " ድንግል ሆይ ስልሽ "

...ለመንገዴ ሰንቅ ነዪ እመቤቴ ለረሀቤ መርሻ ነዪ እመቤቴ

ለታመመ ሰው " ነሽ መፈወሻ "

ለተማጸነሽ " በስምሽ አምኖ "

ማን አፍሮ ያውቃለል " አንቺን ለምኖ "

❾❿ ጎይሌ ብርታቴ

©ዲ/ ታዲዎስ ግርማ

ጎይሌ ብርታቴ ክብሬ ሞገሴ (2)

የዘላለሙ የአብርሃሙ ሥላሴ (2)

...ተመረጠች ነፍሴ አንተን ለማወደስ

ከላይ ከአርያም ከሥላሴ መቅደስ

በአንድነት ሶስትነት በዙፋኑ ሞልቶ

የሚሳነው የለም ለሥላሴ ከቶ

...ከመንገድ ዳር ልቁም የወደቀ ላንሳ

የተራበ ላብላ የታመመ አልርሳ

እንደ አብርሃም አርገኝ እንደ ደጉ አባት

ቤቴ እንዲሞላ ባንተ በረከት

...ጠፈሩን በውሀ በጥበብ የሰራ

እኔስ ይገርመኛል የሥላሴ ስራ

ኑና ተመልከቱ ተአምራት ሲሰራ

ሰዎች እልል በሉ ወላድ ሆነች ሳራ

...አብ አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ወዶናል

ወልድም በተዋህዶ እኛንም መስሎናል

ሃይሉ ተገለጠ የመንፈስ ቅዱስ

በቅዱሳን አድሮ ሲያድን ሲፈውስ

❾❶ገብርኤል ጎያል

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

ገብርኤል ጎያል መልአከ ሰላም መልአከ ብስራት

የምታወጣ የእግዚአብሄርን ህዝብ ከሚነድ እሳት

ፍቅርህ ተስፏል በልባችን

ፊትህ ቆመናል ባርከን ብለን

...የጽናታቸው ዝናው ሲሰማ

ከዚያች ባቢሎን ከሞት ከተማ

ህጻናት ሳሉ በራ እምነታቸው

ቆመህ ተገኘህ መሀከላቸው

...ውህው ሲዘልል ቢያስደነግጥ

በጋኖቹ ውስጥ ቢነዋወጥ

ጸንተው ዘመሩ ልጅ እና እናቱ

አንተ ስትደርስ ከዚያ ከእሳቱ

...ቂርቆስም ጸና ሞትን ሳይፈራ

አንተ ስላለህ ከእነርሱ ጋራ

አትፍሪ አላት ስለምን ትፍራ

አምነው ድል ነሱ ያንን መከራ

...እኔም አምናለው አድነኝ ብዬ

ቆመህ አማልደኝ ከቸር ጌታዬ

ከፉውን ዘመን የማልፍበት

ጽናቱን ስጠኝ ድል ልንሳበት

❾❷ሰዎች እንዘምር

©ዘማሪ ደረጀ ዳመኑ

ሰዎች እንዘምር ለአምላካችን

ከሞት ላወጣን ለአዳኛችን

እናመስግነው እንደ አቅማችን

ምህረት ለሰጠን ለነፍሳችን

...አምላክ ተአምሩን ያሳየብህ

ጩኸት ድምጽህን የሰማልህ

በርጠሜዎስ ሆይ አትተወው

አዳኝ ጌታህን ተከተለው

እውርነቴን ያስቀረልኝ

ለዓይኖቼ ብርሀን የሰጠኸኝ

ሁሌም ከእርሱ ጋር እኖራለው

አዳኜን ትቼ የት እሄዳለው

...በርጠሜዎስ ሆይ ታድለህል

የመዳን ጸጋ ተሰጥቶህል

እጹብ ድንቅ ነው የአምላክ ስራ

እውር የሆነው ዓይኑ በራ

ይህን ጌታዬን ምን ልበለው

ለውለታውስ ምን ልክፈለው

ስሙን ላመስግን ላወድሰው

የአምላክ ክፍያ ይህ ብቻ ነው

...አስራ ሁለት አመት ደም ሲፈስሽ

ሰዎች ሲርቁሽ ሲያንቋሸሹሽ



ከላይ የቀጠለ

ማን ፈወሰሽ አንቺ ሴት

ያበቃሽ ማን ነው ለድህነት

እምነትሽ ኢድኖሻል አለኝ

ኃይል ወጣ ከእርሱ የሚያጽናናኝ

የጌታ ልብሱን ስዳስሰው

ደሜ ቀጥ አለ ላወድሰው

...በቤተ ሳይዳ በአልጋ ስትኖር

በመጠመቂያው በወንዙ ዳር

ድውይ ስትሆን በሽተኛ

እንዴት ተፈወስክ አውጋን ለኛ

አልጋ ታቅፌ ስንገላታ

መዳን ትሻለህ አለኝ ጌታ

አምላኬ እርሱ ፈወሰኝ

አልጋህን ይዘህ ሂድ አለኝ

❾❸ያላንቺ ማን አለኝ

©ዲ/ ልዑልሰገድ ጌታቸው

ያላንቺ ማን አለኝ እመቤቴ

ለተጎሳቀለው ለህይወቴ

እጠራሻለሁኝ ነዪልኝ እናቴ

...ሰውነቴ ሲዝል እመቤቴ መራመድ ሲያቅተኝ ነይ እናቴ

መራመድ ሲያቅተኝ " ኑሮዬ ሲከብደኝ "

ሲያንገዳግደኝ " ችግሬን ተረድተሽ "

ድንግል ሆይ ቅረቢኝ " ድንግል ሆይ ቅረቢኝ "

...በኃጢአት ተይዤ እመቤቴ ጨለማ ሲውጠኝ ነይ አናቴ

የማደርገው ሳጣ " ሲጨንቀኝ ስተጠበኝ "

ባማላጅነትሽ " ዘውትር አትለዩኝ "

...ኪዳነ ምህረት ነሽ እመቤቴ ርህራተ ህሊና ነይ እናቴ

ለሚማጸንሽ ሰው " አትጨክኝምና "

ከልጅሽ ጋር ሆነሽ " ነዪ በደመና "

...እናት እንደ ሌለው እመቤቴ አንገቴን አልደፋም ነይ እናቴ

ተስፋዬ ነሽና " እኔስ አልተከዝም "

ምርኩዜ ነሽና " ከመንገድ አልቀርም "

❾❹አ ሚካኤል

©ዲ/ ዮሐንስ ኤፍሬም

አ ሚካኤል (2) ሊቀ መላእክት

በታጢአት እንዳንወድቅ እንዳንሞት

ፈጥነህ ተራዳን አጽናን በእምነት

...ለያዕቆብ ነገድ ሚካኤል

ለእስራኤል ″

ጠባቂያቸው ነህ ″

መልአከ ሀይል ″

<u>ፍቅርን አድለን ምህረት ቅዱስ ሚካኤል የኛ አባት</u> (2)

...ነጸብራቃዊው ሚካኤል

ተክህኖ ልብስህ ″

ሐመልማለ ወርቅ ″

ዓይኑ ዘርግብ ″

<u>ፍቅርን አድለን ምህረት ቅዱስ ሚካኤል የኛ አባት</u> (2)

...በስእልህ ፊት ሚካኤል

እቆማለሁኝ ″

ፈጥነህ አረጋጋኝ ″

አለው በለኝ ″

<u>ፍቅርን አድለን ምህረት ቅዱስ ሚካኤል የኛ አባት</u> (2)

❾❺መጣው ተከልዬ ልሳለምህ

©ዘማሪት ገነት ህይወት መኮንን

ስምህ ይጠራል በሁሉም ምድር

ሰባኬ ወንጌል የአምላክ ምስክር

ደብረ ሊባኖስ ከመንበርህ

መጣው ተከልዬ ልሳለምህ

...በእጆችህ መስቀል ምድር ተባርካ

ትጠበቃለች በጸሎት ታጥቃ

ውህው አፈሩ ሳሩ ቅጠሉ

ፈውስ ሆኗቸዋል አንተን ለሚሉ

...ሰዳዴ ኢጋንንት ስምህ ሲጠራ

ገድልህ ሲነበብ ሄደ እያጮራ

የአስቦ ጸበል ነፍስ ይቀድሳል

የእጣን መአዛው ሀዘን ያሰረሳል

...መዝገበ ጸሎት ሆኗል ገዳሙ

እርጥቡ ሲነድ በቅዱስ ስሙ

እስራኤል ያየው ሆኗል ቤቴል

ሰማይ ያደርሳል ያ መሰላል

❾❻ሰላም ለኪ እያለ

©ሊ/መ/ ይልማ ሃይሉ

ሰላም ለኪ እያለ (2)

ሐርና ወርቁን ስታስማማ

የገብርኤል ድምጽ ተሰማ

ተሰማ የመልአኩ ድምጽ ተሰማ (2)

...ውሃ ስትቀጂ ክንፉን እያማታ

ሊያበስርሽ የመጣው በታላቅ ደስታ

ከሞገስሽ ብዛት (2) ሲታጠቅ ሲፈታ

አቅርቦልሽ ነበር የክብር ሰላምታ

...የምስራቹን ቃል ምስጢር ተሸክሞ

ገብርኤል ተላከ ሊያረጋጋት ደግሞ

በእርጋታ ተሞልታ (2) ነገሩን መርምራ

የመልአኩን ብስራት ሰማችው በተራ

...ይደሰታል እንጂ መንፈሴ በአምላኬ

በምስጋና ሳድር ዘውትር ተንበርክኬ

ሃሳቤ ለቅስፈት (2) ሌላ መች ያስባል

ለኔ ልጅን መውለድ እንዴት ይቻለኛል

...ካንቺ ሚወለደው ንፁድ ነው ክቡር

የተመሰገነ በሰማይ በምድር

ምስጢሩ ሃያል ነው (2) ይረቃል ይሰፋል

ካንቺ በቀር ይህን ማን ይሸከመዋል

...እጹብ ነው ድንቅ ነው አንቺን የፈጠረ

አንቺን በመውደዱ ሰውን አከበረ

አለም ይባረካል (2) በማጎጸንሽ ፍሬ

ክብርሽን አልዘልቀው ዘርዝሬ ዘርዝሬ

❾❼ቸሩ ሆይ

©ሊ/መ/ቀ/ ምንዳዬ ብርሀኑ

ቸሩ ሆይ ቸሩ ሆይ ናና

ቸሩ ሆይ አማኑኤል ናና

የእስራኤል መና ቸሩ ሆይ ናና

ቸሩ ሆይ አማኑኤል ናና

...ቸሩ ሆይ ለዓይነ ስውር መሪ ቸሩ ሆይ ምርኩዝ መመኪያ ነህ

" አንተን የሚመስል " ምንም ነገር የለም

" ምህረት እና ፍቅርህ " ወሰን ወደር የለው

" ሳንወድህ ወደኸን " ፈልገህ ጠራኸን

...ቸሩ ሆይ አይተህ እንዳላየህ ቸሩ ሆይ ሰምተህ እንዳልሰማህ

" ሁሉን ታልፈዋለህ " ፍቅራዊ አባት ነህ

" አማኑኤል ጌታ " ቸሩ ፈጣሪያችን

" ውለታህ ብዙ ነው " ለኛ የዋልክልን

...ቸሩ ሆይ በከብቶች ማደሪያ ቸሩ ሆይ በዚያች ትንሽ ግርግም

" ተወልዶ አዳነን " ጌታ መድኃኔአለም

" እልል በሉ ሰዎች " በአንድ ላይዘምሩ

" ስብሐት ለእግዚአብሔር " በአርያም በሉ

❾❽ማርያም እንወድሻለን

©ሊ/መ/ቀ/ ምንዳዬ ብርሀኑ

ማርያም እንወድሻለን (2)

ስለወለድሽ የህይወት ምግብን

ማርያም እንወድሻለን

...ድኅሙቴን አትዪ ማርያም በኃጢአት መውደቄን ማርያም

ተስፋዬ አንቺ ነሽ " እስከ እለተ ሞቴ "

ላልከዳሽ ምያለው " ከስርሽ ላልጠፋ "

ገጸ በረከቴ " የህይወቴ ዋስትና "

...የምዕመናን ውበት ማርያም ዘውድ አክሊላቸው ማርያም

ድንግል አንቺ እኮ ነሽ " የመንገድ ስንቃቸው "

ምስክር ነኝ ላንቺ " እንደ ነቢያቱ "

ስጦታ መሆንሽን " ለአዳም ልጆች ሁሉ "

...ሞገስና ጸጋ ማርያም በጌታ ፊት ያለሽ ማርያም

ከሰይጣን መሸሻ " ዋስ ጠበቃችን ነሽ "

እንዴት ነበር ያኔ " ጌታን ስትወልጂው "

የእረኞቹ ደስታ " የመላእክት ዝማሬው "

❾❾አማን በአማን

©ሊ/መ/ ይልማ ሃይሉ

አማን በአማን (2)

አማኑኤል ተመስገን

ለዚህ ፍቅርህ

ምን ልከፈልህ

...ድብቁን ኃጢአት አንተ ብትገልጸው

ይቅር ብለኸኝ ባትሸፋፍነው

እንደ ሰው በቀል ቢኖርህ ጌታ

የኔስ ኃጢአት የለውም ቦታ

...በየ ደቂቃው ኃጢአት ስሰራ

ስሰርቅ ስበድል አንተን ሳልፈራ

አንተ ግን ፊትህ ምንም ቢቀየም

በቁጣ በትር አልገረፍከኝም

...ምህረትን ልከህ አድነኝ ዛሬ

ታክቶኛልና በኃጢአት መኖሬ

ዓለም በኃጢአት እየሳበችኝ

በጽድቅ በደስታ መኖር አቃተኝ

...የኃጠአት ጉዞ ጣፋጭ ቢመስልም

ውጤቱ መሮ ፍጹም አይጥምም

እንደ በደሌ ስላልከፈልከኝ

ተመስገን እንጂ ሌላ ምን አለኝ

❶❶❶ድንግል ማርያም

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ አሰምታ ትናገር ነበር

ሠላም ላንቺ ይሁን አለኝ ቅዱስ ገብርኤል

ሌላ ምንም አላውቅ ያውቃል እግዚአብሄር (2)

...ከመቅደሱ ቁጭ ብዬ ትንቢት እየሰማው

ሐር ወርቅ አሰማምቼ ጥበብ እየፈተልኩ

ሳለው በመገረም ያንን ቃል አሰቤ

አምላክ ሰው ሆነብኝ ተመሰጠ ልቤ

ማን ናት ብዬ ሳሰብ ያቺ ብላቴና

ገብርኤል ደረሰ ብስራቱን ያዘና

ዙፋኑ አደረገኝ የባሪያውን ውርደት ተመልክቷልና

...እንዴት ያለ ማጎጸን ሰማይን ይሆናል

የልዑሉ ዙፋን ወዴት ይተከላል

እያልኩኝ ስጠይቅ በልቤ ለራሴ

የመንፈስ ቅዱስ ሃይል አደረ በራሴ

...እንዴት ከደሀ ቤት ይሄ ንጉሰ ያድራል

ለእርሱ የተገባ ከወዴት ይገኛል

ገሊላን አሰብኳት ዞሬ በህሊና

ለካስ ተሸንፏል በባሪያው ትህትና

...እሳት የማይበላው ሐመልማል አይኖርም

እንዲህ ያለ ቅጠል ናዝሬት አይገኝም

ህሊናዬ መጥቆ ሲበር ወደ ሲና

አንቺ እኮ ነሽ አለኝ ገብርኤለተ መጣና

❶❼❶ የመስቀሉ ፍቅር

©ሊ/መ/ ይልማ ሃይሉ

የመስቀሉ ፍቅር ሲገባን (4)

እመቤታችንን እናያታለን

የመስቀሉ ፍቅር የገባቸው (4)

እመቤታችን ቸለች ከጎናቸው

...አባ ሕርያቆስ አባታችን

የመስቀሉ ነገር ቢገባው

ልቤ አፈለቀ አለ መልካም ነገር

ከድንግል ማርያም ጋር ሲነጋገር (2)

...ለመናኙ ጸሎት ልዩ እጣን

የማሻው ሻማ ነሽ እመ ብርሀን

መዐዛሽ ሸተተኝ ከግሸን

ትናፍቂኛለሽ ምን ልሁን (2)

...ዳዊት በመዝሙሩ ያነሳሻል

የያዕቆብ ድንኳን ነሽ ይልሻል

የእግዚአብሔር ሀገሩ የሚልሽ

እመቤቴ ማርያም አንቺ ነሽ (2)

...ቤተልሔም ስሄድ አይሻለው

ጎልጎታም ስሄድ አይሻለው

ፍጹም አትለዩም ከልጅሽ

የአንቺስ ልዩ ነው ፍቀርሽ (2)

❶❷❷እንዲህ እናምናለን

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

እንዲህ እናምናለን እንታመናለን (2)

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ (2)

አንድ እግዚአብሔር ብለን (2)

...የእግዚአብሔር አብ ፍቅሩ ይረቃል ይሰፋል

ልጁን እስኪ ሰጠን እንዲሁ ወዶናል

በደብረ ታቦር ላይ እርሱን ስሙት ላለው

በመዝሙር ለቃኘን ምስጋና ይድረሰው

...አብርሐም ይስሐቅን አባት እንደ ሆነው

አየደለም ልደቱ በአማን ልዩ ነው

የተወለደ ነው ከቶ አልተፈጠረ

ከአባቱ ጋራ ቅድመ ዓለም የኖረ

...ሊያጽናናን የሚላክ ከአብ የሚወጣው

በሃምሳኛው እለት ወደ እኛ የመጣው

የራሱ የሆነ ፍጹም አካል ያለው

ጰራቅሊጦስ ጌታ እግዚአብሄር አምላክ ነው

...በእደ ዮሐንስ ሲጠመቅ በማይ

ወልድ አምላክ መሆኑን ስንሰማ ከላይ

በአምሳለ ርግብ ወርዶ በእርሱ የሆነው

ለአካላዊው ቃል እስትፋስ ህይወት ነው

❶❼❸ በዘባነ ኪሩብ

©ሊ/መ/ዲ/ ቴዎድሮስ ዮሴፍ

በዘባነ ኪሩብ የሚቀመጠው

በእሳት ድንጋዩ ቅጥሩን ላጠረው

ዘምሩ ለእግዚአብሔር ለጌታ ዘምሩ

የተከበረ ነው በሰማይ በምድሩ

...ኢሳያስ ሲያየው እጅግ አፈረ

የተፈራ ነው የተከበረ

የሰማይ ደጆች ተንቀጠቀጡ

ለቅዱስ ስሙ ክብርን ሲሰጡ

...ያልተደሰተ ለምጽ ያነደደው

እንዴት ይችላል ሊያመሰግነው

በል ፍቀድልኝ ፍቅር ነህና

ልግባ መቅደስህ ላቅርብ ምስጋና

...ዙፋንህ ታየን ትምክቴ ሆይ

ስትመሰገን በሰማይ ላይ

ሳመሰግንህ የተደሰተ

ባይተዋር አልሁን አልውጣ ካንተ

...ቅኔየሞላበት ያንን ሰገነት

ልቀላቀለው ተመኘው በእውነት

ልዘምርልህ ባይገባኝም

ዝም የሚል ልሳን አልሰተኸኝም

❶❼❹አ ማርያም

አ ማርያም ምልእተ ጸጋ

ጌታ ሲመጣ እኛን ፍለጋ

በማህጸንሽ አደረብሽ

የአምላክ እናት ደስ ይበልሽ

...በዛፍ በቅጠሉ እርግቦች መጡና

ሲጎራረሱ አየች ሐና በጥሞና

እናት እርግቢቱ ልጇን ስታጎርሰው

መካኒቱ ሐና ጀመረች ማልቀሱን

...የሐናን ልመና እግዚአብሔር ሰማና

ፍሬዋን ለገሳት በፍጹም ትህትና

የነቢያት ትንቢት ማርያም ስትወለድ

ምሰሶ ኃጢአታችን ይኸው ታየ ሲናድ

...የድንግል መወለድ ቢያስደስታቸው

መላእክት ወረዱ በሽብሸባቸው

በመላእክት ሀገር ዝማሬ ተሰማ

በድምቀት አበሩ ኢዮርና ራማ

...ለተራበ ምግቡ ለታረዘ ልብሱ

ለኃጢአተኛው ወገን ለመናኙ ስንቁ

ተወለደችለት ብላቴናይቱ

የዮሴፍ ሽልማት የሙሴ ጽላቱ

❶❼❺እመቤቴ ማርያም

እመቤቴ ማርያም (4)

ካንቺ ተወለደ የሰራዊት ጌታ

እመቤቴ ማርያም ይድረስሽ ሰላምታ

...ህይወቱን የሰዋ ፍጹም ለሰላም

ሁሉንም የሚችል ያለ በአርያም

<u>የአምላክ ማደሪያ ድንግል ማርያም</u> (2)

<u>ጌታ የመረጠሽ እስከ ዘላለም</u> (2)

...የምድር ባለ ጸጎች ሲማልዱ ፊትሽ

የሰማይ መላእክት ዝማሬ ያቅርቡልሽ

<u>አህዛብ ይንበርከኩ ለሃያሉ ልጅሽ</u> (2)

<u>ክብር ይገባሻል በእናትነትሽ</u> (2)

...ላንቺ ሊያስተላልፍ ገብርኤል ሰላምታ

ከ ንጉ

❶❶❻ይቄድሰዋ

ይቄድሰዋ መላእክት (2) ለማርያም

በውስተ ውሳጤ መንጦላይት ወይብልዋ በሃኪ ማርያም ሃዳስዩ ጣእዋ

❶❶❼ክነፈ ርግብ

ክነፈ ርግብ በብሩር ዘግቡር ወገበዋቲሃኒ በሐመልማለ ወርቅ

አንቲ ምስራቅ ወወልድኪ ጸሀየ ጽድቅ አማን በአማን (2) ኢየሀልቅ ኪዳንኪ ወላዲተ አምላክ

ትርጓሜ

እንደ ርግብ ክንፍ በብርም እንደ ተሰራች ጎኖችሽም የወርቅ ሐመልማል

አንቺ ምስራቅ ልጅሽም የጽድቅ ጸሀይ ነው እውነት በእውነት (4) ኢያልቅም ቃልኪዳንሽ የአምላክ እናት

❶❶❽ነአምን በአብ

ነአምን በአብ ወነአምን በወልድ በወልድ

ወነአምን (5) በመንፈስ ቅዱስ

ትርጓሜ

እናምናለን በአብ እናምናለን በወልድ በወልድ

እናምናለን (5) በመንፈስቅዱስ

❶❶❾የኪዳን ጽላት

የኪዳን ጽላት የተሰወረ መና ያለብሽ ደብተራ መሰዋእት አንቺ ነሽ

ይኧውም መና የተባለው (2) በድንግል ማርያም ያደረው

የእግዚአብሔር አብ ልጁ ነው

❶❶❿አንቲ ውእቱ

አንቲ ውእቱ ተስፋሁ ለአዳም ኪዳነ ምህረት

አመ ይትሰደድ እም ገነት (2)

ትርጓሜ

አንቺ ነሽ ተስፋው ለአዳም ኪዳነ ምህረት

በተሰደደ ጊዜ ከገነት (2)

❶❶❶ያከበርዋ ለሰንበት

ያከበርዋ ለሰንበት መላእክት በሰማያት ጻድቃን በውስተ ገነት

ወኩሉ ፍጥረት አሳት ወአናብርት እለ ውስተ ደይን ያዕረፉ ባቲ እሰመ ባቲ አዕረፈ እምኩሉ ግቡር

❶❶❷ቤዛ ቤዛ

ቤዛ ቤዛ ለኢትዮጵያ ንጉስ መድኃኒአለም

ለዝክረ ስምኪ (3) ወላዲተ አምላክ

❶❶❸አባ ማርቆስ

አባ ማርቆስ አባ ማርቆስ

በጸሎቱ ተአምረ ገብረ

❶❶❹ርኢክዋ ለቤተክርስቲያን

ርኢክዋ ለቤተክርስቲያን አፍቀርክዋ ለቤተክርስቲያን

ዘኢትዮጵያ (2) ቤተክርስቲያን

ትርጓሜ

አየውህት ቤተክርስቲያንን ወደድኳት ቤተክርስቲያንን

የኢትዮጵያን (2) ቤተክርስቲያን

❶❶❺ኢትዮጵያ ታበጽህ

ኢትዮጵያ ታበጽህ እደዊሀ እደዊሀ ሃበ እግዚአብሔር

እንዘ ትብል አምላኪየ አምላኪየ ነጽረኒ ወአድኅነኒ እም እደ ጸላኢ ወጸር

❶❶❻ኪሮስ አቡነ

ኪሮስ አቡነ

አቡነ አርከ አምላክ (2)

❶❶❼አባ አባ

አባ አባ ገብረ መንፈስ ቅዱስ

ሃበ አምደ ወርቅ (2) ስሙ ጽሁፍ (2)

❶❶❽ለሀገሪትነ ሰላማ

ለሀገሪትነ ሰላማ ኪያከ ተአቅብ

አባ አ አባ (2) ገብረ መንፈስ ቅዱስ (2) አባ

❶❶❾ለተ/ሃይማኖት ጻዲቅ

ለተ/ሃይማኖት ጻዲቅ መጠነ በዛ ህማሙ

ትዌድሶ ደብረ ሊባኖስ ገዳሙ (2)

እስመ በውስቴታ ተገብረ ፍልሰተ ስጋሁ ወአጽሙ

ትዌድሶ ደብረ ሊባኖስ ገዳሙ (2)

እምነ አድባራት ኩሎን እንተ ለአለት በስሙ

ትዌድሶ ደብረ ሊባኖስ ገዳሙ (2)

ኢየሱስ ክርስቶስ እንተ ቀደሳ በደሙ

ትዌድሶ ደብረ ሊባኖስ ገዳሙ (2)

❶❷❿ነይ ነይ

ነይ ነይ ማርያም ወላዲተ አምላክ የጻድቃን እመቤት የመላእክት እህት

ሁላችሁ እመኗት ከልብ አማላጅ ናትና በእውነት እናመስግናት እናወድሳት አማላጅ ኪዳነ ምህረት

❶❷❶እመቤታችን ማርያም

እመቤታችን ማርያም ሀገራችንን ጠብቂልን በምልጃሽ

ከመናፍቃን ከከሃድያን ከጠላት ሰይጣን ሰውረሽ እንድትጠብቂን በምልጃሽ

❶❷❷አ አባ

አ አባ ቅዱስ እቀቦሙ በስምከ ወበ ሃይልከ እቀቦሙ

ከመ ይኩኑ አሐደ ብነ ከማነ (2)

❶❷❸መሰረተ ዜማ

መሰረተ ዜማ ወጠነ ወጠነ ያሬድ ካህን

ያሬድ (4) ካህን ጥዑመ ልሳን

❶❷❹ሰቢኮ ለወልድ

ሰቢኮ ለወልድ (2) ትንሳኤ ሞቱ

ያሬድ ወረሰ መንግስቱ (2)

❶❷❺ጊዮርጊስ ሃያል

ጊዮርጊስ ሃያል ሃያል መስተጋድል

ገባሪ ተአምር (2) ኮከበ ክብር

❶❷❻መልአከ ሰላምነ

መልአከ ሰላምነ ሊቀ መ

ላእክት ሚካኤል

ሰአል ወጸሊ በእንቲአነ አዕርግ ጸሎተነ ቅድመ መንበሩ ለመድኃኒአለም

❶❷❼ካህናት ይብልዋ

ካህናት ይብልዋ ይብልዋ ለማርያም

ሰላም ለኪ (4) ይብልዋ ለማርያም

❶❷❽እምነ እምነ

እምነ እምነ ንዒ (2)

በሰላም በሰላም ንዒ ማርያም

❶❷❾ንጽህይተ ንጹሀን

ንጽህይተ ንጹሀን ከዊና ከመ ታቦር ዘዶር ዘሲና ውስተ ቤተ መቅደስ ነበረት በድንግልና ነበረት

ሲሳያ ህብስተ መና ወሲቲ ሃኒ ስቲ ጽሙና

ጌቱዮን ! ! !

በ ይምርጎነ ክርስቶስ (መንግስተአብ ብርጎነ)

†††

2010